## የፍቅር፡ወሬ።

ልጅ፡ይስታ፡ለሳምንታ፡ለጥቂት፡እሱም፡ለሳምንታ፡ከሰጠው፡በኋላ፡ወንድሜ፡ሆይ፡የዚህ፡ሐውልት፡ምሥጢሩ፡ምንድነው፡ብትተረጉምልኝ፡እወዳለሁ፡አለው።

ያም፡አርቲስት፡የዚህ፡ሐውልት፡ትርጉም፡የታወቀ፡ነው። ሰው፡ሁሉ፡እንደረዳ፡ይተረጉመዋል፡ነገር፡ግን፡እኔ፡እንደሚመስለኝ፡ልተረጉምልህ፡እችላለሁ።

እነዚህ፡ከወንዝ፡ዳር፡ተቀምጠው፡የሚሳሳሙ፡ሁለት፡ሰዎች፡የዕለት፡ወዳጆች፡ናቸው። ለሱም፡ሌላ፡ወዳጅ፡አለው፤ ለሷም፡ሌላ፡ወዳጅ፡አላት።

ከላይ፡ሆኖ፡እያሳቀ፡የሚመለከታቸው፡ሽማግሌ፡ሕሊናቸው፡ነው።

ሰው፡መሠረት፡ያለው፡ፍቅር፡ከሌለው፡ወደድኩህ፡ወደድኩሽ፡ቢባባሉም፡ፍቅር፡ስለሌላቸው፡ሕሊናቸው፡እንደሚስቅባቸው፡





የፍቅርና፡የሐሳብ፡ብርቱ፡ፈረስ።

ያሳስባል።

ይህ፡ሐውልት፡ጥሩ፡ስለምግባር፡ሰዎች፡ሁሉ፡በዓይን፡ማየት፡ብቻ፡የሚያስተምር፡ጥበባዊ፡ሐውልት፡ነው፡አላቸው።

ከዚህ፡በኋላ፡ልጅ፡ዩስታና፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡እጅ፡ለጅ፡ተያይዘው፡የዚሁኑ፡ነገር፡እየተጫወቱ፡በአቨኑ፡ዱሎፒራ፡በኩል፡አድርገው፡ወደ፡ፕላስ፡ዱላኮንኮርድ፡ሔዱ።

ከዚያም፡ወደ፡ሻንዜሊዜ፡አቋርጠው፡ሲሔዱ፡አንድ፡ሰው፡ካንድ፡ትልቅ፡ፈረስ፡ጋር፡ሲጓተቱ፡ከሰውየው፡ጉልበት፡የፈረሱ፡ጉልበት፡፲፪፡ጊዜ፡ስለሚበልጠው፡ስቦ፡ጐትቶ፡ሲወስደው፡የሚያሳይ፡ትልቅ፡ሐውልት፡አዩ።

ወይዘሮ፡ውቢቱ፡አባክህ፡ይህንን፡የሚነገርም፡ሐውልት፡ተጠግተን፡እንየው፡ስላለችው፡ሁለቱም፡ተጠግተው፡ቆመው፡ይመለከቱ፡ጀመር።





ልጅ፡ዩስታ፡አባክሽ፡ፍቅሬ፡ይህ፡ሐውልት፡የምን፡ምሳሌ፡ይመስልሻል፡ብሎ፡ጠየቃት።

ወይዘሮ፡ውቢቱም፡የዚህን፡ምሳሌ፡ማንም፡ሰው፡ሊያውቀው፡ይችላል።

ይህ፡ሰው፡የኔና፡ያንተ፡ምሳሌ፡ነው፡ፈረሱም፡ካቅማችን፡በላይ፡የሆነው፡ፍቅራችን፡ነው።

ሰውየው፡አለቅም፡ብሎ፡ጠንክሮ፡እንደያዘው፡እኛም፡ከብዙ፡ጊዜ፡ጀምረን፡ሳንሰለች፡ሳናቋርጥ፡መከራና፡ኀዘንም፡ቢመጣብን፡ሳያሰቅቀን፡እስካሁን፡መቆየታችንን፡ያስረዳል።

እንደገና፡ደግሞ፡ፍቅራችን፡ሲያጠብቅ፡በማድ፡ጐትቶ፡እንደሚወስደን፡ያስረዳል፡አለችው።

ልጅ፡ዩስታ፡ተሰማ፡እቅፍ፡አድርጎ፡ሳመ፡

የኔ፡ፍቅር፡የኔ፡ባትሆኚ፡እንዴት፡ባዘንኩ፡ልክ፡እውነተኛ፡ትርጉሙ፡ይህ፡ነው።

እንግዲህ፡ወደ፡ቤታችን፡እንሒድ፡ብሎ፡የወይዘሮ፡ውቤቱን፡እጅ፡ይዞ፡በሸንዢሌዢ፡በኩል፡የፍቅር፡ጫወታቸውን፡እየተጫወቱ፡አሸኑ፡ሆሽ፡በሚባለው፡ጉዳና፡ውስጥ፡ገብተው፡ወደ፡ሆቴላቸው፡ደረሱ።

ነገር፡ግን፡ወደ፡ራት፡ያለ፡ነገር፡ሁሉ፡ይደርሳል፡እንደተባለው፡እንደ፡ወር፡ካሥር፡ቀን፡በደስታ፡የተቀመጡት፡ቀን፡በቶሎ፡አለፈ።

የደስታ፡ቀን፡ከጠመንጃ፡ተኩስ፡ይበልጥ፡ትፈጥናለች፡እንደተባለው፡ያለፈውን፡ሁሉ፡ደስታ፡የመለያያቸው፡ቀን፡ኀዘን፡ደመሰሰው፡የቀቢፀ፡ተስፋ፡ወለሚ፡ወደቀባቸው፡ጥር፡፳ቀን፡፲፱፻፲፮፡ዓመተ፡ምሕረት።

ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ጉብሬ፡ክምሪስ፡ተነሥታ፡በባቡር፡ተሳፍራ፡ማርሴይ፡ሆቴል፡ነዋይ፡ገባች።






ልጅ፡ደስታ፡ተሰማም፡በሌላ፡ባቡር፡ማታ፡በ፫ሰዓት፡ተነሥቶ፡ማለዳ፡በ፲፩ሰዓት፡ማርሴይ፡ደረሰ።

መርከቡ፡ከእኩለ፡ቀን፡በኋላ፡በ፲ሰዓት፡የሚነሣ፡ስለሆነ፡ጥቂት፡ሰዓት፡ለመነጋገር፡ጊዜ፡ስላገኙ፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡ኢስጥላንዲድ፡ሆቴል፡ሆኖ፡ለወይዘሮ፡ውቤቱ፡ሆቴል፡ንዋይ፡ስልክ፡ደወለላትና፡ባንድ፡ታክሲ፡ብቻዋን፡መጥታ፡የመጨረሻ፡ስንብታቸውን፡በለቅሶ፡ተሰናበቱ።

አሥር፡ሰዓት፡ሲሆን፡ወይዘሮ፡ውቤቱን፡ሊሸኙ፡የመጡ፡የሌጋሲዮን፡ሹማምንቶችና፡ማርሴይ፡ያለው፡ኰንሱል፡አኖሬር፡ስለ፡ፈረንሳዊ፡መንግሥትም፡እንደ፡ሹም፡ተከትለዋት፡ሔዱ።

ልጅ፡ደስታም፡አንድ፡ታክሲ፡ይዞ፡ከነሱ፡ኋላ፡ለመሸኘት፡ተከትሏት፡ነበር።



የሜሳጀሬ፡ማሬቲም፡መርከብ ።

## የፍቅር፡ወሬ።

ወይዘሮ፡ውቤቱም፡ከመርከቡ፡ከወጣች፡በኋላ፡ሽኚዎቹ፡ከመርከቡ፡ሳይ፡ወጥተው፡የስንብት፡ሰላምታቸውን፡ሊሰጡ፡ልጅ፡ደስታም፡አብሮ፡ሰላምታ፡ሊሰጥ፡ዕንባዋ፡ባይጋ፡መሌቆ፡እጁን፡ይዞ፡ጥቂት፡ከቆየች፡በኋላ፡ደህና፡ሁኚ፡ደህና፡ሁን፡ተባብለው፡ተለያዩ።

ከዚህ፡በኋላ፡ሁሉም፡ከመርከብ፡ወርደው፡መርከቡ፡ጠረፉን፡እስኪለቅ፡ድረስ፡ቆመው፡ሲጠባበቁ፡የመሐደ፡ምልክት፡ሲነሩ፡የሁለቱም፡ልብ፡በኀዘን፡ተነክቶ፡ዕንባቸው፡ያለልክ፡እንደ፡ጐርፍ፡ይወርድ፡ነበር።

ከሁሉም፡የሚያሳዝነው፡ሽኚዎቹ፡ሁሉ፡ሐዲውን፡እሱን፡ልጅ፡የምስራች፡ቆመው፡መርከቡ፡ካይን፡እስኪጠፋ፡ድረስ፡ይመለከቱ፡የነበረው፡ነው።

## ፫ ምዕራፍ።

ከዚህ፡በኋላ፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡በኀዘን፡

የፍቅር፡ውሬ።

ተወብጦ፡እንደ፡ቆሰለ፡ሰው፡ሕሊናው፡ዝሎ፡
በሚያሳዝን፡አኳኋን፡ወደ፡ሆቴሉ፡ተመለሰ።

ከማርሴይ፡ተመልሶ፡ፓሪስ፡ከገባ፡ወዲ
ህ፡እንዲሁ፡ያለ፡ኀዘን፡ወደቀበት፡ይመስልሃል፡
የተያያዘ፡ያጥንቱና፡የደሙ፡ፍቅር፡ያሳት፡ጎ
ደኛው፡ተለይታ፡ስትሔድበት፡ከነፉን፡እንደ፡
ተመታ፡አሞራ፡የሚሔድበት፡ቦታ፡ቸግሮት፡
ብቻውን፡ከመኝታ፡ቤቱ፡ዘግቶ፡ይቀመጥ፡ነበር።

ያ፡ከወይዘሮ፡ውቤ፡ጋር፡ሆኖ፡ያየውን፡
ታሪካዊ፡ቦታ፡ሁሉ፡በዓይኑ፡ለማየት፡ጠላው።

ጥቂት፡የሚያጽናናው፡ከልጅ፡የምሥራ
ች፡ጋር፡የሰዋን፡ወግ፡መጫወት፡ብቻ፡ነበር።

ከዚህ፡በኋላ፡ፓሪስ፡ጥቂት፡ቀን፡ከተቀመ
ጠ፡በኋላ፡የፓሪስን፡ሥራ፡ወርሶ፡ወደ፡ሎንዶን፡እ
ንዲሔድ፡ከመንግሥቱ፡ትእዛዝ፡ደረሰው።

ለልጅ፡ደስታ፡ሎንዶን፡መሔድ፡በጣም፡ደ





የእንግሊዝ፡ፓርላማ።

የፍቅር፡ወሬ።
ስ፡አለው። ምክንያቱም፡ ምረስ፡ከለዋ፡ጋር፡ የተቀመጠበትን፡ ሠቴልን፡ አብረው፡ የሔዱበትን፡ ቦታ፡ በማየት፡ ጓዘኑ፡ ኢየባሰበት፡ ስለሔደ፡ ተጨንቆ፡ ነበር።

ሎንዶን፡ የተረጥሮ፡ ያገሩ፡ ቅዝቃዜና፡ የሕዝቡ፡ ጸጥ፡ በራድነት፡ ሳዘነ፡ ልብ፡ የተስማማ፡ ስለሆነ፡ ተጽናና። ቢሆንም፡ ወይዘሮ፡ ውቢቱ፡ ደብዳቤ፡ ሳትጽፍ፡ በመቅረቷ፡ ምን፡ ሆና፡ ይሆን፡ በማለት፡ ይጨነቅ፡ ነበር።

ከሁለት፡ ወር፡ የማይበልጥ፡ ቆይቶ፡ እንደ፡ ደብዳቤና፡ እንደት፡ የተጠቀለለች፡ ሣጥን፡ በሬኮማንዴ፡ ደረሰው።

ልጅ፡ ደስታ፡ ደብዳቤውን፡ ሲከፍተው፡ በደስታና፡ በፍርሃት፡ ይንቀጠቀጥ፡ ነበር።

አንቮልኩን፡ ከቀደደው፡ በኋላ፡ የፍቅሩ፡ የወይዘሮ፡ ውቢቱ፡ ደብዳቤ፡ በመሆኑ፡ ጠጠን፡ የሌለው፡ ደስታ፡ ደስ፡ አለውና፡ ደብዳቤውን፡





የንክሰን፡ኰለም ።

እየሳመ፡ካነበበ፡በኋላ፡መልሱን፡ይጽፍ፡ጀመ
ር።

## ፲፪ኛ፡ደብዳቤ።

እጅግ፡የማፈቅርሽ፡እኅቴ፡ካገርሽ፡ደህና፡መድረስሽን፡የጻፍሽልኝን፡ደብዳቤ፡ባነበብኩ፡ጊዜ፡የናፍቆት፡ዕንባ፡ሳላስበው፡ካይኔ፡ፈሰሰ። ይልቁንም፡አንችን፡በማጣቴ፡በቤቴ፡ውስጥ፡መሽ፡አደረ፡እንግዳ፡ሆኜ፡ተቀምጫለሁ። አንችን፡በማሰብ፡ሰውነቴ፡ፈዞ፡ስለምታይ፡የሚወዱኝ፡ሰዎች፡ሁሉ፡ከፈረንጅ፡አገር፡ሐዲ፡መድኃኒት፡አድርገውባት፡መጣች፡እያሉ፡እንዲ፡በሽተኛ፡ያዝኑልኛል፡ብለሽ፡የጻፍሺውን፡ስመለከት፡እምሆነውን፡ነገር፡አሳጣኝ።

ፍቅሬ፡ሆይ፡እኔም፡ካንቺ፡የባሰ፡ነገር፡ደርሶብኛል። ፓሪስን፡የመሰለ፡ከተማ፡አንቺ፡ከሔድሽ፡ወዲያ፡ያባቴን፡ግዳይ፡ስለመሰለኝ፡ብዙ፡ጊዜ፡ከመኝታ፡ቤቴ፡ብቻየን፡ዘግቼ፡እውል፡ነበር።





ነገር፡ግን፡አዘንተኞችን፡የሚያጽናና፡ቸሩ፡እግዚአብሔር፡ሥራሰን፡ለቅቄ፡ወደ፡ሎንደን፡እንድዛወር፡መንግሥቴ፡ጻፈልኝ።

ስለዚህ፡ካንቺ፡ከማፈቅርሽ፡ጋር፡ያሳየሁት፡ከተማ፡በመሆኑ፡ትንሽ፡ተጽናናሁ። ይልቁንም፡ያንቺ፡ደብዳቤ፡ስለ፡ደረሰኝ፡የበለጠ፡ኀዘኔን፡አሻሻለልኝ።

የኔ፡ፍቅር፡የጀመርነው፡መሠረት፡ከነፋስና፡ከጐርፍ፡ጋር፡ለመጋፋት፡ስለሆነ፡ምባባራችንንና፡ሰውነታችንን፡ማበርታት፡ያስፈልጋል። ወደ፡ፊትም፡ብዙ፡ጠላቶች፡እንደሚነሡብን፡የታወቀ፡ነው። ጻድቅ፡ሰው፡እንደ፡ደቦል፡አንበሳ፡በመንገድ፡ብቻውን፡ቢሄድ፡ማንንም፡አይፈራም፡እንደተባለው፡እኛም፡የፍቅርን፡አምላክ፡ይዘን፡ወደፊታችን፡እንድንገፋ፡የምግባር፡ብርታትና፡የሰውነት፡ጥንካሬ፡ያስ

ፈልገናል። በኀዘን፡ተወንቀን፡ብንኩራመት፡ ለጠላት፡ በፈሣጆችን፡ተማርከን፡እጆችንን፡እ ንጂ መስጠት፡ያለ፡ነው።

የኔ፡ፍቅር፡አንቺ፡በማዘንሽ፡ጠላትሽን፡ አሣበርቺ። ሰውነትሽንም፡አታጕሳቍሊ፡የሳ ክሺልኝም፡የወርቅ፡ማስታወሻ፡የመድኃኒታ ችን፡ሥዕል፡የተቀረፀበት፡ደረሰኝ።

የኔ፡ፍቅር፡እንዲንቺ፡ክደረቴ፡ሳይ፡የ ማይለየኝ፡ባልንጀራ፡ስለላክሺልኝ፡በጣም፡ አመሰግንሻለሁ።

እኔም፡ሌልክልሺ፡ያሰብኩትን፡በነጭ፡ ወርቅ፡በአልማዝ፡እንደ፡ልብ፡የተሠራ፡እን ገትሽ፡ሳይ፡እንድታደርጊው፡ልኬልሻለሁ። ይኸውም፡እንደ፡ልብ፡የተሠራው፡ጌጥ፡በአ ለማዙ፡በኩል፡ሲከፍቱት፡ውስጡ፡ሣጥን፡ ስለሆነ፡በመካከሉ፡ከኢየሩሳሌም፡ኅንቺ፡ያ መጣሁልሽ፡በሰም፡ካይ፡ጌታችን፡የተሰቀለበት፡





ዕንጨት፡ቅራሬ፡ተለጥፎበታል። በበኋቹም፡ በማይታወቅ፡በጣም፡ረቂቅ፡በሆነ፡ጽሕፈት፡ የኔና፡ያንቺ፡ስም፡ተሳስሮ፡ተቀርፆበታል።

ስለዚህ፡የፍቅራችን፡መታሰቢያ፡ጠ ባቂሽ፡ስለሆነ፡ለማንም፡እንዳትሰጪ፡አደ ራሺን።

የኔ፡ፍቅር፡ነፍስ፡በተነሣ፡ጊዜ፡እሳት፡ አይሞቁሩም፡እንደሚባለው፡የኔና፡ያንቺ፡ነገ ር፡ጥቂት፡ጥቂት፡ሳይሰማ፡አይቀርምና፡ በ ምንጸጸፈው፡ደብደቤ፡ነገር፡በጣም፡ተጠንቀ ቂ፡ አደራሽን። የፍቅር፡አምላክ፡በደኅና፡እን ያኘችን፡ለመጠወቅ፡ያብቃን። ነሐሴ፡፲፱፡ቀን፡ ፲፱፻፷፩፡ዓመተ፡ምሕረት ።

በጣም፡የማፈቅርሽ፡

ደስታ፡ተሰማ ።

፲፩ኛ፡ ደብዳቤ ።

እጅግ፡የማፈቅርህ፡ወንድሜ፡የሳኩብኝን፡

ደብዳቤ፡ ባነበብኩት፡ ጊዜ፡ አንተን፡ ያገኘሁህ፡ መሰለኝ፡ ደስ፡ አለኝ።

የላክልኝም፡ እንደ፡ ልብ፡ በአልማዝና፡ በነጭ፡ ወርቅ፡ የተሠራ፡ መቍስቢያ፡ ደረሰኝ።

ይልቁንም፡ የመድኃኒታችን፡ መስቀል፡ ተፍቆ፡ በውስጡ፡ ተስጥሮ፡ ያገኛል፡ በስሁ፡ ስለደፍክልኝ፡ እንግዲህ፡ ሳይ፡ አይርገው፡ ዘወትር፡ ያጽናናኛል።

ስለዚህ፡ ከፍ፡ ባለው፡ ስጦታህ፡ በጣም፡ አመሰግንሃለሁ። የኔ፡ ናፍቆት፡ እኛ፡ ወደዲስ፡ አበባ፡ ለመሔድ፡ እንደራጀን፡ ከባለቤቴም፡ ከደጅዝማች፡ መስፍን፡ ጋር፡ ከሮም፡ ከተመለስኩ፡ ወዲህ፡ ልባችን፡ ተራርቋል።

እኔም፡ አንተን፡ በማሰብ፡ ሰውነቴ፡ ሁሉ፡ ስለዛለ፡ በቤቴ፡ ውስጥ፡ እንደሌለሁ፡ እቆጠራለሁ። የልቤን፡ ጭንቀትና፡ ናፍቆት፡ ጥቂት፡ የሚያስታግሥልኝ፡ ያንተን፡ ደብዳቤዎች፡ ማንበብ





ና፡ የሰጠኸኝንም፡ ፎቶግራፍ፡ መሳም፡ ብቻ፡ ነው።

የኔ፡ ናፍቆት፡ ካንተ፡ ጋራ፡ መገናኘቱና፡ አብሮ፡ መኖር፡ ሳስበው፡ ጥቅጥቅ፡ ያለ፡ ጨለማ፡ ሆኖ፡ ይታየኛል።

አባክህ፡ የኔ፡ ፍቅር፡ ስንቱን፡ ሰንቅሩት፡ ዘለን፡ ስንቱን፡ ወጥመድ፡ አምልጠን፡ እንገባ፡ ይሆን።

እውቃለሁ፡ በእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ሁሉ፡ ይቻላል። አሁን፡ በቅርብ፡ ቀን፡ እንደ ሰማሁት፡ በከተማው፡ የኔና፡ ያንተ፡ ፍቅር፡ በግልፅ፡ ይወራል፡ ይባላል።

እኛ፡ እንደገንባ፡ ጉዳዩን፡ ከፍ፡ ወዳለ፡ ፖለቲካ፡ አዙረውታል፡ ብሎ፡ ወንድሜ፡ ነገረልኝ። ባሌም፡ በኔ፡ ላይ፡ ለመበቀል፡ የጥፋት፡ ማስረጃ፡ ይፈልጋል።

ቢሆንም፡ የጻፍክልኝን፡ ወረቀት፡ እ

ንጹ ያገኘው፡ ለታመነ፡ አሽከሬ፡ በሣጥን፡ ቱ ልኬ፡ ሰጥቼው፡ በታመነ፡ በቃ፡ አስቀምጦ ታል።

አሁንም፡ የምንጽፈው፡ ደብዳቤ፡ በ ባሌ፡ እጅ፡ እንዳይወድቅ፡ መጠንቀቅ፡ ስለ ሚያስፈልግ፡ እኔ፡ አዲስ፡ አበባ፡ ደርሼ፡ እኅ ቴን፡ እስክጽፍልህ፡ ድረስ፡ ደብዳቤ፡ አት ጻፍልኝ። ይህንንም፡ የምጽፍልህ፡ በጣም፡ አ ያዘንኩ፡ ነው።

ምክንያቱም፡ ያለኝ፡ ተስፋ፡ አጽናኜ ያንተ፡ ደብዳቤ፡ ብቻ፡ ነበር። የኔ፡ ናፍቆት፡ እ ግዚአብሔርን፡ ረዳትህ፡ ይሁን፡ ከማለት፡ በ ተቀር፡ ምን፡ ማድረግ፡ እንችላለን። መስከ ረም፡ ፪ቀን፡ ፲፱፻፷፪፡ ዓመተ፡ ምሕረት።

በጣም፡ የምታፈቅርህ፡

ውቢቱ፡ ገብሬ።

አንባቢ፡ ሆይ፣ ልጅ፡ ደስታ፡ በዚህ፡ ደብ





ዳቤ፡ ምክንያት፡ በጣም፡ አዘነ። ምክንያ ቱም፡ የናፍቆቱን፡ ግለት፡ የሚያበርድለት፡ ከሚያፈቅራት፡ ወዳጁ፡ መልስ፡ ማግኘት፡ ብቻ፡ ነበር።

ይልቁንም፡ በሁለቱ፡ ፍቅር፡ ምክንያ ት፡ የቤት፡ ዘመድ፡ ጠብ፡ ባዲስ፡ አበባ፡ ውስ ጥ፡ በጣም፡ በተገለጠ፡ እኅቷን፡ መስማቱን፡ ለለሳካችበት፡ ለመጋባታቸው፡ ዕንቅፋት፡ ይፈጥር፡ ይሆን፡ በማለት፡ ነው።

ከዚህም፡ በተቀር፡ ደብዳቤ፡ ከመጻፍ፡ እንዲጠነቀቁ፡ ስለጻፈችለት፡ ምናልባት፡ የ ፍቅር፡ ደብዳቤያቸውን፡ በጠላት፡ እጅ፡ ገብቶ፡ ይሆን፡ በማለት፡ ተጨነቀ።

ይህንኑ፡ ቀንም፡ ሌትም፡ በማሰብ፡ ድን ገት፡ ራስ፡ የሚያዞር፡ በሽታ፡ ወደቀበትና፡ ወ ደ፡ ሐኪም፡ ቤት፡ ወሰደው፡ አስተኙት።

እሱም፡ አእምሮውን፡ አጥቶ፡ ልሑ፡ ድ፡

እያለ፡ ይቃጅ፡ ነበር። እንደ፡ስምንት፡ቀ
ን፡ ያህል፡ከታከመ፡በኋላ፡ጥቂት፡ተሻለው።

## ፪ ምዕራፍ።

ከዚህ፡ በኋላ፡ ወዲጁ፡ ልጅ፡የምስራች፡
ከምሬት፡መጥቶ፡ አየውና፡በጣም፡አዝኖ፡ወ
ዲጁ፡ ደስታ፡ በምን፡ምክንያት፡ ይመስልሃ
ል፡እንዲህ፡ያለ፡በሽታ፡የወደቀብህ፡ብሎ፡
ጠየቀው።

ልጅ፡ ደስታ፡ እኔም፡ ሐመሜን፡ምን፡እን
ደሆነ፡አላወቅሁትም፡ብቻ፡ወይዘሮ፡ውቢ
ቱ፡ተስፋ፡የሚያስቆርጥ፡ደብዳቤ፡ስለጻፈ
ችልኝ፡ መንፈሴ፡ በጣም፡ታውኮ፡ነበር።

ሲጀምረኝ፡ራቴን፡በልቼ፡ ወደ፡መኝታ፡
ቤቴ፡ ስሔድ፡ራሴን፡ አዞረኝ፡ ወደቅሁ።

ከዚያ፡በኋላ፡ወደ፡ሲሳ፡ዓለም፡ሐጂ፡ነ
በር።





ልጅ፡የምስራች፡ ወዴት፡ሔደህ፡ኖር
ዋል። ልጅ፡ ደስታ፡ተሰማ፡ ወንድሚ፡ሆ
ይ፡ ሰጣውት፡ በጣም፡ይገርምሃል፡ ወይዘ
ሮ፡ ውቢቱ፡ ወደገርዋ፡ከተመለሰ፡ ለመሸኘት፡
ሔደን፡ማርሴይ፡ከባሕሩ፡ዳር፡ቆመን፡መር
ከቡ፡ሲጓዝ፡ስንመለከት፡ከነበረው፡ስፍራ፡
ሔጄ፡ቆሜ፡ በሩቁ፡እመለከት፡ ይመስለኛ
ል። በዚያን፡ጊዜ፡በምሥራቅ፡በኩል፡ሙ
ሉ፡ጨረቃ፡ወጥታ፡ስለነበረ፡የጨረቃው፡ብር
ሃን፡ከባሕሩ፡ ላይ፡ሲያበራ፡ ልቤን፡አሸበረው።

ባሕሩም፡ በማዕበልና፡በሞገድ፡ሲወ
ጣና፡ ሲወርድ፡ ከጨረቃው፡ብርሃን፡ጋር፡ ል
ቤን፡ በናፍቆት፡ማዕበል፡ አማታው።

ከዚያው፡ቆሜ፡ስመለከት፡ወይዘሮ፡
ውቢቱን፡ በጨረቃው፡አጠገብ፡ቆማ፡አየኋት።

በዚያን፡ጊዜ፡የኔ፡ፍቅር፡ቆይኝ፡ወደንቺ፡
መጣሁ፡ብዬ፡ዘልዬ፡ከባሕሩ፡ውስጥ፡ገብቼ፡

ኦዋኝ፡ ፮ መር።

ጥቂት፡ እየዋኘሁ፡ እንደሔድሁ፡ ማዕበሉና፡ ሞገዱ፡ ሲወጣና፡ ሲወርድ፡ በፍጥነት፡ ለመሔድ፡ በጣም፡ አወከኝ።

የሐሊም፡ ፋጫ፡ ሆሞብኝ፡ ወደ ፊት፡ ለመድረስ፡ ስፍጨረጨር፡ ጨረቃዋ፡ ጠለቀች። ወይዘሮ፡ ውቢቱም፡ ተሠወረችኝ።

በዚያን፡ ጊዜ፡ የደረሰብኝ፡ ጭንቀት፡ ይህ፡ ነው፡ ለማለት፡ አይቻልም።

እኔም፡ ተስፋ፡ ቆርጬ፡ ከማዕበሉና፡ ከሞገዱ፡ ጋር፡ ስታገል፡ ስወጣ፡ ስወርድ፡ ዓሣዎቹ፡ በላዬ፡ ላይ፡ ሲዘሉ፡ እንዳንድ፡ ጊዜም፡ ገፍተው፡ ሲጥሉኝና፡ ስሰጥም፡ ስወጣ፡ በሚያስፈራው፡ ድቅቅ፡ ጨለማ፡ ስንገላታ፡ ከሀገሬ፡ ጠረፍ፡ የደረስሁ፡ ይመስለኛል።

ሌጅ፡ የምሰራች፡ እንደምን፡ የሚገርም፡ ነገር፡ ነው፤ እባክህ፡ ወንድሜ፡ ከዚያ፡ በኋላ፡





እንደምን፡ ሆንህ።

ከዚህ፡ በኋላ፡ የምሥራች፡ ፀሐይ፡ ወጣች። ወዲያው፡ እየሞቀ፡ ሔደ።

እኔም፡ በብርድ፡ ሰውነቴ፡ ቀዝቅዞ፡ እንደ፡ በረዶ፡ ሆኖ፡ ነበርና፡ ሙቀቱ፡ ተስማምቶኝ፡ ሰውነቴም፡ ተፍታታ።

ወዲያው፡ ወደገሬ፡ ከተማ፡ ለመሔድ፡ ጉዞ፡ ጀመርሁ።

የበረሃው፡ ሙቀትና፡ ያሸዋውና፡ የዱቡሌቱ፡ ማጥ፡ እያሰከዱም፡ ብሎኝ፡ ባሳር፡ በመከራ፡ ከከተማው፡ አቅራቢያ፡ ደረስሁ።

ከጣቢያው፡ ሳይ፡ ዘበኛ፡ ቁሞ፡ ሲጠብቅ፡ ኝ፡ ጥሮ፡ ወደኔ፡ መጥቶ፡ ስምህ፡ ማነው፡ ብሎ፡ ጠየቀኝ።

እኔም፡ ደስታ፡ ተሰማ፡ እባላለሁ፡ አልሁት። እሱም፡ ወደ፡ ከተማ፡ እንዳትገባ፡ ክልክል፡ ነህ፡ ብሎ፡ አስታወቀኝ።

## የፍቅር፡ወሬ።

ከዚህ፡በኋላ፡እያዘገኩ፡ለከተማው፡ምሥራቅ፡የሆነች፡ርስት፡ስላለችኝ፡ወደዚያ፡እጓዝ፡ጀመር።

ሌኪ፡በሁለት፡ሰዓት፡ከቤቱ፡ደረስሁ።

ልጅ፡የምስራች፡እንደምን፡ሌብን፡የሚነካ፡ታሪክ፡ነው፡እባክህ፡ተጥል።

ልጅ፡ደስታ፡ከርስቴ፡ላይ፡ጥቂት፡ዓመት፡የተቀመጥሁ፡ይመስለኛል፡ከዕለታት፡አንድ፡ቀን፡ወደማታ፡ትልቅ፡የሚያስደነግጥ፡መዓት፡ተነሥቶ፡መሬቱ፡ሁሉ፡ይንቀጠቀጥ፡ጀመር።

ይህ፡ነገር፡ምን፡ይሆን፡ብዬ፡ተራራው፡ባትራቢያዬ፡ስለሆነ፡መነጽሬን፡ይዤ፡ከተራራው፡ማፍ፡ወጣሁና፡ወደከተማው፡ሰመለከት፡ከተማው፡ተሸብሮ፡ቤቶችና፡ሕፃናቶች፡ሽማግሌዎች፡መጮረሻ፡አጥተው፡ሲፈፈጡ፡ነፋስ፡ምንጭ፡መብረቅ፡ከሰማይ፡ሲወ



ያጼ፡ምኒልክ፡መታሰቢያ፡ሐውልት።

የጥቅር፡ወሬ።

ር ጅ፡እያየሁ፡ተመነትሁ።

ጎቲት፡ቶያቶ፡ከተማው፡በሙሉ፡ተቋጠለ። ወዲ፡ምድር፡ባቡር፡መጋቢያው፡ሬት፡ለሬት፡የቆመው፡የእንበሳው፡ሐውልቱና፡የስሙ፡ጥሩው፡ንጉሥ፡ሐውልት፡በነሩሰና፡በመሬት፡መንቀጥቀጥ፡ምክንያት፡ተነቅለው፡ከአሬር፡ሳይ፡ወደቁ።

የመናገሻው፡ቤተ፡ክርስቲያንም፡በእሳት፡ሲቃጠል፡ነበልባሉ፡ታየኝ።

አይቻችው፡የማላውቅ፡የውጭ፡አገር፡ወታደሮች፡ሐፃናትን፡እጃችውን፡እየያዙ፡በእሳት፡ነበልባል፡ውስጥ፡ሲጥሉዋቸው፡አየሁ።

ብዙ፡ሽማግሌችም፡ከቤታቸው፡መውጣት፡ስላልቻሉ፡ከነጆቸው፡ጋር፡እብረው፡ተቃጠሉ።

ተራራዎችም፡ሁሉ፡በዚሁ፡መዓት፡ተን





የቅዱስ፡ጊዮርጊስ፡ቤተ፡ክርስቲያን።

ደው። ወደቁ።

በሳያችው ም፡እሳተ፡ገሞራ፡ ወጣ።

ሰው ም፡እርስ፡በርሱ፡በፉስ፡በጐራዴ፡ በውቤ፡በጦር፡በጠመንጃ፡ተያይዞ፡ሲቷገል፡ ደሙ፡እንደ፡ጐርፍ፡ሲፈስ። እኔም፡የከተማ ይቱን፡መቃጠልና፡ያገሬን፡ጥፋት፡እያየሁ፡ ሳለቅስ፡የቃጠሎው፡እሳት፡ከተማውን፡ጠ ለል፡አድርጎ፡ያሳይ፡ጀመር።

ወደ ያው፡መነጽሬን፡አውጥቼ፡ስመ ለከት፡የደጃዝማች፡መስፍን ሠንገሽ፡ፈጅ የው ጭ፡አገር፡መንግሥት፡ባንዲራ፡ይዞ፡የጥንት የሮማውያንን፡ሌብስ፡ለብሶ፡እያቻቸው፡የ ማሳውቅ፡የውጭ፡አገር፡ወታደሮች፡አስከት ሎ፡ሕዝቡን፡ባካፋ፡በደማ፡ሲጨፈጭፉቸው፡ አየሁ።

ከዚህ፡በኋላ፡ራሴን፡ደገኜ፡ወደ፡አገሬ፡ ወደ፡ፍትሬ፡ውቤት፡ወደ፡ባለቤቴ፡ወደ፡ልጅ





ቼ፡እያልኩ፡ወኬ፡አለቀስሁ።

ደልቱንም፡በጣም፡ያዘንሁት፡ፍቅሬ፡ ወደዘሮ፡ውቤት፡ከደጃዝማች፡መስፍን፡ል ጅ፡ጋር፡በኔ፡ምክንያት፡ከፍ፡ያለ፡ጠብ፡ስላ ሳቱ፡በሱ፡እጅ፡የወደቀች፡እንደሆን፡እንደ ምን፡ያለ፡ሥቃይ፡ይደርስባት፡ይሆን፡በማ ለት፡ነው።

ልጅ፡የምሰራች፡ወንድሚ፡ሆይ፡በዚ ህ፡መጣት፡በሆነው፡ቅዠትህ፡ምክንያት፡ያ ንግጠህ፡ብገን፡አለማለትህ፡ይገርማል።

ልጅ፡ደስታ፡የተወደድህ፡ወንድሚ፡ሆ ይ፡እንቅልፍ፡ቢሆን፡በዚህ፡ሥቃይ፡ምክን ያት፡ብንን፡አል፡ነበር።

ይህ፡የማጫውትህ፡እንቅልፍ፡አይደለ ም። ከታመምሁ፡ጀምሮ፡ሐመሚ፡እስከ፡ለ ቀቀኝ፡ድረስ፡አእምሮዬ፡ጠፍቶ፡ማንንም፡ አላውቅም፡ነበር። ማንም፡ቢመህ፡ከእንቅል

የፍቅር፡ወሬ።

ሬ፡ሌሊያነቃኝ፡አይችልም፡ነበር።

ልጅ፡የምስራች፡በጣም፡ይገርማል፡ አባክህ፡ወንድሜ፡ጨወታህን፡ቀጥል።

ልጅ፡ዲስታ፡ይህ፡የእሳት፡ማዕበልና፡ ጉርፍ፡ወደ፡ምሥራቅ፡ሲያመራ፡በአትራቢያዩ፡ያለ፡ተራራ፡መንቀጥቀጥ፡ጀመረ።

ስለዚህ፡ከተራራው፡ጫፍ፡ወርጄ፡እሽቱ፡ልቂዩ፡እሮጥ፡ጀመር።

ጥቂት፡እልፍ፡እንዳልኩ፡አንድ፡ሰው፡ እንደኔው፡ሲሸሽ፡ተገናኘን፡ቆሞ፡እንዲያነጋግረኝ፡ለመንኩት።

እሱም፡ከዚህ፡መዓት፡ለማምለጥ፡ችኩያለሁና፡የምትጠይቀኝ፡ነገር፡እንዳለ፡ ጠይቀኝና፡ከዚህ፡ከጥፋት፡ከተማ፡ሳምልጥ፡አለኝ።

እኔም፡ወንድሜ፡ከተማችንን፡የሚያቃጥለው፡ማነው፡ብዬ፡ጠየቅሁት።





የሃይማኖት፡ጦርነት።

እሱም፡የቡኤል፡ዜቡል፡ሠራዊቶች፡ናቸው፡ይባላል። እኒሆም፡ንጉሡ፡ወዴት፡ሔዱዋል፡ብዬ፡ብጠይቀው፡ንጉሡማ፡በጦር፡ግንባር፡ሳይ፡ሔደ፡ከቡኤል፡ዜቡል፡ሠራዊት፡ጋራ፡ሲዋጋ፡የንጉሡ፡ሠራዊት፡በጠላት፡ፍላፃና፡መርዝ፡ያርበኝነቱ፡ምግባር፡ስለ ወደቀ፤ ይልቁንም፡በመብረቅና፡በነጐድጓድ፡ምክንያት፡ተራራዎቹ፡ስለወደቁ፡ንጉሡ፡ብቻውን፡ሰይፉን፡መዞ፡አርበኞች፡ሆይ፡ንጉሣችሁንና፡አገራችሁን፡ጥላችሁ፡ወዴት፡ትሔዳላችሁ፡እያለ፡ከሬሳ፡ላይ፡ቆሞ፡እነውራሱ፡አይቼዋለሁ።—

ነገር፡ግን፡ከዚያው፡ይቀር፡ወይም፡ይዳን፡አይታወቅም። እንደኔ፡ሐሳብ፡መሬትዋ፡ከድንቷ፡የሕዝቡ፡ልብ፡ተሸብሮ፡ተራራው፡ሁሉ፡በመብረቅ፡ይናድ፡ስለነበረ፡ከዚያው፡ከመሬቱ፡ላይ፡ወድቆ፡የቀረ፡ይመስ





ለኛል።— የእግዚአብሔርን፡ተአምር፡ግን፡ማንም፡አያውቀውም።—

ወንድሜ፡እንግዲህ፡ከዚች፡በቀር፡ጊዜ፡የለኝምና፡ደኅና፡ሰንብት፡ብሎ፡ግሳጋራው፡ከወደ፡ኋላው፡እንደሚያሳድደው፡ሰው፡ይሮጥ፡ጀመር።—

እኔም፡ወደ፡በረሃው፡አቈልቍዬ፡እሮጥሁ። እንደ፡ጊዜም፡ሳሳርፍ፡ሌትና፡ቀን፡ሰበር፡ሰወድቅ፡ስነሣ፡ከውጋዴን፡በረሃ፡ደረስሁ።—

እንደአጋጣሚ፡ውጋዴን፡ሳይ፡ትልቅ፡ጦርነት፡ሆኖ፡ደረት፡ለደረት፡ተያይዞው፡ሲፋጁ፡ደረስሁ።—

ግማሹ፡በሳንጃ፡ሌሎቹም፡በፋስና፡በጦር፡በጕራዴ፡እንዲያውም፡ምንም፡መሳሪያ፡የሌለው፡አንገቱን፡አንቆ፡በጥርሱ፡ጕሮሮውን፡ይቆርጠው፡ነበር።—

በዚያ፡በበረሃ፡ውስጥ፡የሰው፡ልጅ፡ደም፡እንደ፡ጐርፍ፡ፈሰሰ። ፀሐይም፡ጨለመች። በጦሩም፡ሜዳ፡ላይ፡የሞት፡ጥላ፡ወደቀበት።

እኔም፡ካንድ፡ከፍ፡ካለ፡ቦታ፡ቆሜ፡ስመለከት፡እንደ፡ከዚህ፡ቀደም፡የማውቀው፡በህብትና፡በማዕርግ፡ከፍ፡ያለ፡ሰው፡ከሙም፡ባለሰሳት፡በሰው፡ብዙ፡የሚባል፡የቡኤል፡ዜቡልን፡ምልክት፡አድርጎ፡ደም፡የተቀባ፡ፋሱን፡በቀኝ፡እጁ፡ይዞ፡ወዲኔ፡መጣና፡እንተ፡ከሐዲ፡ብሎ፡ሰደበኝ።

እኔም፡ከሐዲ፡እንተ፡ነህ፡የቡኤል፡ዜቡል፡ባሪያ፡ብዬ፡መለስኩለት።

እሱም፡ተንደርድሮ፡ራሴን፡በፋሱ፡ሊመታ፡ሲቃጣ፡ዘልዬ፡ቀኝ፡እጁን፡ያዝሁት።

በግራ፡እጁም፡ወገቤን፡ይዞ፡ስንተናነቅ፡ሁለታችንም፡ካንድ፡ፈፋ፡ውስጥ፡ወደ





ቀብን።

እሱ፡በላዬ፡ሁኖ፡እኔም፡ቀኝ፡እጁን፡እንደያዝሁ፡አገጨን፡በራሱ፡እየመታ፡ጉሮሮዬን፡በጥርሱ፡ለመበጠስ፡ሲጥር፡እኔም፡ለመከላከል፡ራሴን፡ወደ፡ደረቱ፡ሳገባ፡ጡቱን፡አጋጠመኝና፡የላዩና፡የታቹ፡ጥርሶቼ፡ሥጋውን፡አልፈው፡እስኪጋጠሙ፡ድረስ፡ነከስሁት።

የዚያን፡ጊዜ፡ጮሆ፡ፋሱ፡ከጁ፡ወደቀ። እኔም፡የክርስቶስ፡ባሪያ፡ብዬ፡ፎክሬ፡ከላዩ፡ላይ፡እንሥቼ፡ወደ፡መሬት፡ጥዬ፡በገዛ፡ፋሱ፡ራሱን፡መታሁት።

በዚያን፡ጊዜ፡ደሙ፡በልብሴ፡ላይ፡ተረጨብኝ። ልጅ፡የምስራች፡አምንት፡ሰብሮ፡የሚገባ፡ጫወታ፡ነው፡እንደምን፡ያገርማል። ከዚህ፡በኋላ፡እንደምን፡ሆነ።

ልጅ፡ደስታ፡ብቻዬን፡ከራሱ፡ላይ፡ቆሜ፡

በውድቀት፡ጨለማ፡ነፍሳቸው፡ያልወጣውን፡ሰዎች፡ሲያንቋርሩ፡ሲንፈራገጡ፡እየሰማሁ፡የፍርሃት፡እንቅጥቅጥ፡ይዞኝ፡ግራና፡ቀኝ፡እንሳመጥ፡ነበር።

ከጥቂት፡ጊዜ፡በኋላ፡ሩሱን፡ከሬሳው፡ላይ፡ወርውሬ፡ወደ፡ሬቱ፡አሮጥ፡ጀመር።

ነገር፡ግን፡የወንድሞቼ፡ሬሳና፡የደሙ፡ጉርፍ፡አሳስኪዱ፡አለኝ።

ያሌቁትም፡የወደቀውን፡ሬሳ፡ለመብላት፡የተሰበሰቡ፡ተናጣቂ፡አውሬዎች፡ወዲያና፡ወዲህ፡ሲያቋርጡ፡አሁን፡አሁን፡በሉኝ፡እያልኩ፡እየሮጥሁ፡ስመሀ፡ወደ፡በረሃው፡ውስጥ፡ገባሁ።

ባሸዋውና፡በድቡልቅኙ፡ምክንያት፡ስወድቅ፡ስነሣ፡ካንድ፡ባሕር፡ጠረፍ፡ደረስሁ። በሩቁ፡ስመለከት፡እንዲት፡መርከብ፡ሬቅ፡ብላ፡ከባሕሩ፡ውስጥ፡ቆማ፡አየሁ።





መርከብዋንም፡እየተመለከትሁ፡አገሬ፡የቡኢሌዚቡል፡አገር፡ሆና፡ከማየት፡በዚች፡መርከብ፡ተሳፍሬ፡ከባዕድ፡አገር፡ሔጄ፡መሞት፡ይሻለኛል፡አዬ፡ጉድ፡አገርን፡በጫማ፡ውስጥ፡ይዞ፡መሔድ፡አይቻልምን፡ብሎ፡ዲንቶን፡የሚባል፡ሰው፡የተናገረው፡እንደምን፡ያለ፡አስተዋይ፡ነው፡እያልኩ፡ሳስብ፡አንድ፡ሱማሌ፡በትንሺ፡ጀልባ፡ላይ፡ሆኖ፡ወደኔ፡ሲመጣ፡አየሁት።

እሱም፡ከጀልባው፡ወርዶ፡ሰላምታ፡ከሰጠኝ፡በኋላ፡እባክህ፡ወንድሜ፡ከዚያ፡ከምናየው፡መርከብ፡አድርሰኝ፡ብዬ፡ለመንሁት።

እሱም፡ማድረስ፡እደርስሃለሁ።ነገር፡ግን፡እኩሉ፡ሌሊት፡ስላለፈ፡ዋጋው፡እጥፍ፡ነው፡አለኝ።እኔም፡ግድ፡የለም፡እከፍልሃለሁ፡ምን፡ያህል፡ነው፡ብዬ፡ጠየቅሁት።

## የፍቅር፡ወሬ።

እሱም፡ አምስት፡ መቶ፡ ፍራንክ፡ ነው፡ አለኝ።

እኔም፡ በፍጥነት፡ ከኪሴ፡ አውጥቼ፡ ሰጠሁትና፡ ከጀልባው፡ ሳይ፡ አሳፍሮኝ፡ ይዞኝ፡ ሔደ።

መርከቡም፡ ከጠረፉ፡ ራቅ፡ ብሎ፡ ሰለ፡ ቆመ፡ በውድቅት፡ ጨለማ፡ የመርከቡን፡ መብራት፡ በማየት፡ ብቻ፡ ነፋሱ፡ ሰለከፋ፡ ባሕሩ፡ በጣም፡ መጥፎ፡ ሆኖ፡ ታውክ፡ ስለነበረ፡ በማዕበሉና፡ በጭጋጉ፡ ስንወጣና፡ ስንወርድ፡ በጭንቅና፡ በመከራ፡ ከመርከቡ፡ አጠገብ፡ ደረስን።

ነገር፡ ግን፡ መርከቡ፡ መሰላሉን፡ ስላልፈታ፡ መውጫ፡ አጣሁ። ሱማሌውም፡ እንመለስ፡ ቢለኝ፡ አይሆንም፡ ብዬ፡ ተቃወምኩት።

ነፋሱም፡ እየበረታ፡ ይሔድ፡ ጀመር፡ አንዳንድ፡ ጊዜም፡ ወደ፡ ውቅያኖሱ፡ ለመውሰድ፡





የመከራ፡ ሌሊት ።

ደንፋን፡ነበር።

ስለዚህ፡ሱማሌው፡በጣም፡ተበሳጭቶ፡እግዚአብሔር፡ከተቆጣው፡ሰው፡ጋራ፡እንጥሞኝ፡መከራዬን፡አየሁ፡እያለ፡ይመረር፡ነበር።

ከጥቂት፡ጊዜም፡በኋላ፡እነኚ፡ማጀራቴን፡በድንገት፡ይዞ፡ከባሕር፡ጥሎ፡ለመለስ፡ቆረጠና፡እዘገጃቶ፡ማጀራቴን፡ይዞ፡ወደ፡ባሕሩ፡ሊጥለኝ፡ሲል፡እኔም፡ፎክሬ፡ጉሮሮውን፡አነቅሁት።

ሁለታችንም፡ከጀልባው፡ላይ፡ስንታገል፡ከጀልባው፡ውጪ፡አስወጥቼ፡ልጥለው፡ስገፋው፡ከባሕሩ፡ላይ፡ወድቆ፡የጀልባውን፡ዳር፡በጁ፡ይዞ፡ገለበጠውና ሁለታችንም፡ከባሕሩ፡ላይ፡ወደቅን።

ጀልባይቱ፡ግን፡ወዲያው፡ትንሳፈፍ፡ጀመር። ነገር፡ግን፡መሬ፡ስለሌላት፡ከመር





ከቡ፡ውጪ፡በነፋሱ፡እየተገፋች፡ራቀች።

ሱማሌው፡ግን፡በጣም፡ዋና፡ስለሚያውቅ፡እየዋኘ፡በብዙ፡ድካም፡ደረሰባትና፡በጀልባው፡ላይ፡ወጥቶ፡ወደ፡ጠረፉ፡በፍጥነት፡ተመለሰ።

እኔ፡ግን፡በመርከቡ፡አጠገብ፡እየዋኘሁ፡ኡ፡ኡ፡የሰው፡ያለህ፡ነፍስ፡አድኑ፡እያልኩ፡እጮህ፡ነበር።

ነገር፡ግን፡በመርከቡ፡ላይ፡ያሉት፡መኰንኖች፡የሚበዙት፡ከውስጥ፡ዳንስ፡ያደርጉ፡ነበርና፡ለመስማት፡አልቻሉም። የተረፉትም፡በድልድዩ፡ዙሪያ፡በእግራቸው፡ይናፈሱ፡ነበርና፡ምንም፡አላስተዋሉም። እኔ፡ግን፡በጣም፡ደክሞኝ፡ተስፋ፡ቆርጬ፡ነበር። ቢሆንም፡ኡ፡ኡ፡የሰው፡ያለህ፡ነፍስ፡አድኑ፡እያልኩ፡መጮኼን፡አላቋረጥሁም፡ነበር።

ነገር፡ግን፡እንዴት፡ሴት፡በረንዳው-
ን፡ተደግፋ፡ተክዛ፡ባሕሩን፡ስትመለከት፡
የሰው፡ድምፅ፡መሆኑን፡ስላወቀች፡እን
ት፡ሰው፡ምንድነው፡የምትለው፡ብላ፡በ
ትጠይቀኝ፡በነፋሱና፡በማዕበሉ፡ምክን
ያት፡አልሰማኋትም። እከዋ፡ግን፡ሉ፡ሉ-
ማለቷን፡ጥቂት፡ጥቂት፡ትሰማ፡ነበርና፡
ሮጣ፡ሔዳ፡አንድ፡ሰው፡ከመርከቡ፡ላይ፡
ወድቆ፡ይመሃልና፡አድኑት፡ብላ፡ነገረች
ችው።

እነሱም፡ወጥተው፡ብቅ፡ብለው፡ቢ-
መለከቱ፡በባሕር፡ላይ፡ሰ ዋኝ፡አዩኝ።

የዚያን፡ጊዜ፡ቶሎ፡ብለው፡ገመድ፡
ወረወሩልኝና፡ባሳር፡በመከራ፡ገመዱን፡አ
ገኘሁት።

ነገር፡ግን፡ገመዱን፡ይዤ፡መውጣት፡
ስላልቻልኩ፡ቶሎ፡ብለው፡ከወገቤ፡ላይ፡እ





ሥሬ፡እባካችሁ፡ጐትታችሁ፡አውጡ-
ኝ፡ እያልኩ፡ስጮህ፡እነሱም፡አውቆ፡ይወ
ጣል፡ብለው፡ይጠብቁኝ፡ነበር።

ነገር፡ግን፡ብዙ፡ጊዜ፡ከጠበቁ፡በኋላ፡
ይህ፡ሰው፡ራሱ፡ለመውጣት፡አልቻለም፡
ብለው፡ጐትተው፡አወጡኝና፡ከድልድዩ፡
ላይ፡አስተኙኝ።

ከዚያ፡በኋላ፡ሐኪም፡መጥቶ፡መረ
መረኝ። ወዲያው፡ጥያቄ፡ጀመረ። እንተ፡
ከዚህ፡መርከብ፡ውስጥ፡የነበርክ፡ሠራተ
ኛ፡ነህን፧ እኔም፡አይደለሁም፡እኔ፡የውጭ
አገር፡ሰው፡ነኝ፤ አገሬ፡በእሳት፡ስለተቃጠ
ለች፡ያገሬን፡ጥፋት፡ከማየት፡በውጭ፡አ
ገር፡ስደተኛ፡ሆኜ፡መሞትን፡ስለመረጥሁ፡
በዚች፡መርከብ፡ተሳፍሬ፡እንድሔድ፡ያን
ድ፡ሱማሌ፡፳ ልባ፡ትክራይቼ፡መጥቼ፡ነበ
ር። ሱማሌው፡በነፋስና፡በማዕበሉ፡ስለ

ተንገላታ፡ተቆጥቆጦ፡እኔን፡በባሕር፡ላይ፡
ጥሎኝ፡ተመልሶ፡ሔደ።

ሐኪሙም፡አገርህ፡ወዴት፡ነው፡ብ
ሎ፡ጠየቀኝ። እኔም፡አገሬ፡ኢትዮጵያ፡ነ
ው፡ብዬ፡ስመልስ፡ያቺ፡ውኸቲን፡ሰምታ፡
የጦር፡መኰንኖችን፡የጠራችልኝ፡ወይዘ
ሮ፡ውቢቱ፡ፕሬ፡ከዚያ፡ቆማ፡ትመለከት፡
ነበርና፡ወደኔ፡ተጠግታ፡አንተ፡ማነህ፡አለ
ችኝ። እኔም፡ዴስታ፡ተሰማኝ፡አልኋት።

በዚያን፡ጊዜ፡አንገቴን፡በጆሮ፡ብድ
ጋ፡አድርጋ፡የኔ፡ፍቅር፡ከየት፡መጣህ፤ከሰ
ማይ፡ወረድህን፡እያለች፡ትስመኝ፡ነበር።

የዚያን፡ጊዜ፡ከጃንሆይ፡ቤት፡የነበሩ
ት፡መኰንኖች፡ሁሉ፡ወጥተው፡እየተመ
ለከቱ፡እንዲት፡ስመ፡ጥሩ፡ወይዘሮ፡ይህን
ን፡አድርጋም፡ሰው፡አንገቴን፡አቅፋ፡በመሳ
ምዋ፡ናቷት።





እንዲንዶችም፡ምን፡ይሆን፡ይህ፡ነገር፡
እያሉ፡ተደንቀው፡ቆመው፡ይመለከቱን
በር።

ጥቂት፡ደቂቃ፡እየተሳቀሰን፡ከቆየን፡
በኋላ፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡ከኔ፡ርቃ፡ቆማ፡ክ
ቡራን፡ወንድሞቼ፡ሆይ፡ቸር፡እግዚአብ
ሔር፡ያደረገልኝን፡የተአምራት፡ሥራ፡ስ
ገልጥላችሁ፡የደስታ፡ዕንባ፡እያነቀኝ፡ስለ
ሆነ፡ይቅርታ፡እንድታደርጉልኝ፡እለምና
ለሁ።

ይህ፡ከፊታችሁ፡ተጐሳቁሎ፡ደክሞ፡
ጠቁሮ፡ልብሱ፡በደም፡ተወማልቆ፡የምታ
ዩት፡ሰው፡የኔ፡ፍቅሬ፡አወኛዋ፡ነው።

ነገር፡ግን፡የጋብቻችን፡ሥነ፡ሥርዓት፡
እንዳይፈጸም፡የመንግሥት፡ፖለቲካ፡ገብ
ቶ፡በት፡ተቋረጠ።

ይህ፡አርበኛ፡አንጉ፡በብኤል፡ዚቡ

ሌ፡ ጦር፡ ተወሬ፡ ስለ፡ ሀገሩ፡ በጦር፡ ሜዳ፡ ላ
ይ፡ ሲዋጋ፡ የጦሩ፡ ምግባር፡ ስለወደቀ፡ በ
ጠላት፡ እጅ፡ ከመውደቅ፡ ይልቁንም፡ የነ
ግ፡ ሞት፡ ከመለማት፡ ተሰይፎ፡ በውሎ፡ አገ
ር፡ መሞት፡ ይሻለኛል፡ ብሎ፡ በዚች፡ መርከ
ብ፡ ተሳፍሮ፡ ለመሔድ፡ የመጣ፡ ነው፡ እንጂ፡
ተራ፡ ሰው፡ እንዳይመስላችሁ፡ ብላ፡ አስታ
ወቀቻቸው።

## ፲፫ ምዕራፍ።

ከዚህ፡ በኋላ፡ ሁሉም፡ ተደንቀው፡ ካፒ
ቴኑ፡ ልብሴን፡ እንዲያጥቡልኝና፡ እንዲያ
ደርቁልኝ። እኔንም፡ እንዲያሞቁኝና፡ ሴነ
ጋ፡ ጤሜን፡ እንዲሳውኝ፡ ትእዛዝ፡ ሰጥቶ፡
ወደ፡ አንድ፡ ካቢን፡ ወሰደው፡ አስተኙኝ።

ማለዳ፡ ጤሜን፡ ተሳልቼ፡ ልብሴን፡ ለ
ብሼ፡ ከፍቅሬ፡ ከወይዘሮ፡ ውቢቱ፡ ጋር፡ ከው





ጭ፡ ከዕንጨት፡ ወንበር፡ ላይ፡ ተቀምጠ፡ ያ
ለፈውን፡ ታሪክ፡ ስንጫወት፡ የጦር፡ መኰንኖ
ቹ፡ እያዩ፡ ትሳንት፡ ማታ፡ ሰናየው፡ እንደም
ን፡ ያስጠይፍ፡ ነበር። ለካ፡ በመጉሳሳት፡ ኖር
ዋል፡ እንደምን፡ ያለ፡ የሚያምር፡ ወጣት፡ ነ
ው፡ እያሉ፡ ያመሰግኑኝ፡ ነበር።

ቁርሳችንንም፡ ከበላን፡ በኋላ፡ ካፒቴ
ኑ፡ ወይዘሮ፡ ሆይ፡ እንግዲህ፡ መርከቡ፡ ለመ
ሔድ፡ ሰዓቱ፡ ደርሷልና፡ ወዳጅሽን፡ አሰናብ
ቺውና፡ ይመለስ፡ ብሎ፡ አስታወቃት።

ወይዘሮ፡ ውቢቱም፡ እባክህ፡ ከኛ፡ ጋር፡
ለመሔድ፡ አይችልምን፡ ቢፈቀድለት፡ እን
ደምን፡ ደስ፡ ባለኝ፡ አለችው።

እሱም። ወይዘሮ፡ ሆይ፡ ምንም፡ ቢሆ
ን፡ አይቻልም። ምክንያቱም፡ የጦር፡ መርከ
ብ፡ ስለሆነ፡ እንጂ፡ የንጉሥ፡ ቤት፡ ስብ፡ በመሆ
ንሽ፡ በልዩ፡ ፈቃድ፡ የተደረገ፡ ነው፡ እንጂ፡ ለሌ

ሳ፡ ሰው፡ አይፈትድም፡ አሳት።

እንግዲያው፡ እንደምን፡ ለመምጣ ት፡ ይችላል፡ እያለች፡ ታለቅስ፡ ጀመር።

ካፒቴኑም፡ በጣም፡ አዝኖ፡ እኔ፡ ያደ ሬ፡ ወረቀት፡ እሰጥዋለሁ። ያለጥርጥር፡ በ መጀመሪያው፡ መርከብ፡ ይመጣል፡ እመኚ ኝ፡ ብሎ፡ ወደ፡ ቢሮው፡ ገብቶ፡ ወረቀቱን፡ ጽ ፎ፡ አመጣልኝና፡ ሰጠኝ።

እኔም፡ እንግዲህ፡ ፍቅሬ፡ ልውረድ፡ እ ልኩና፡ አንገት፡ ላንገት፡ ተያይዘን፡ ተሳስመ ን፡ መንገድ፡ ስጀምር፡ ቆይ፡ የኔ፡ ፍቅር፡ ብላ፡ የጣትዋን፡ አልማዝ፡ አውልቃ፡ ይህን፡ ሸመ ዩ፡ ተሳፍረህ፡ በቶሎ፡ ና፡ አለችኝ።

እኔም፡ የኔ፡ ፍቅር፡ ጥልቅ፡ የሆነ፡ አሳብ፡ ስለአሰብሺልኝ፡ በጣም፡ አመሰግናለሁ።

ይህ፡ ከፍ፡ ያለ፡ ዋጋ፡ ያለው፡ የከበረ፡ ድ ንጋይ፡ ለከበሩ፡ ሰዎች፡ ነው፡ እንጂ፡ ገንዘብ፡ የ





ሚሆነው፡ ለእንደኔ፡ ያለ፡ ድሀ፡ ግን፡ መክራና፡ ጥፋት፡ እንዲሚሆንብኝ፡ አታውቂምን።

ይህ፡ ዕቃ፡ በኔ፡ በድሀ፡ ላይ፡ ሲታይ፡ ባላጋ ራ፡ ከሳሽ፡ ሆኖ፡ ሌባ፡ መባልን፡ ስም፡ ከመሰ ጠቱ፡ በተቀር፡ ጠቃሚ፡ እንዳይሆነኝ፡ የታወ ቀ፡ ነው።

ስለዚህ፡ ካስታወስሺኝ፡ ምንም፡ የም ሳፈርበት፡ ገንዘብ፡ ስለሌለኝ፡ ትንሽ፡ ገንዘብ፡ ስጪኝ፡ አልኋት።

እስዋም፡ የሚበቃ፡ ገንዘብ፡ ስለሌላት፡ ከኮሮጆዋ፡ ውስጥ፡ አውጥታ፡ አምስት፡ ሺህ፡ ፍራንክ፡ ሰጠችኝና፡ አንገት፡ ላንገት፡ ተያይዘ ን፡ ተሳሳምንና፡ ከመርከቡ፡ ወርጄ፡ ባንዲት፡ ጀልባ፡ ወደ፡ ወረፉ፡ ተመለስሁ። እስዋም፡ በመርከብ፡ ሔደች።

ልጅ፡ የምስራች፡ ይህ፡ የምታጫውተኝ፡ በውነት፡ በሕልምህ፡ ቅጀት፡ ያየኸው፡ አይመ

የጥቅር፡ወሬ።
ስለኝም። ምናልባት፡እንድ፡ልብ፡ወለድ፡ታሪ
ክ፡መጽሐፍ፡የምታጣውትኝ፡ይመስለኛል
አለው።


ልጅ፡ዩስታ፡ከት፡ብሎ፡ስቆ፡ወንድሟ
ለኔም፡ያገርመኛል። ሳንተ፡ለወንድሟ፡ባይ
ሆን፡ለማንም፡ሰው፡አሳጣውትውም፡ነበር።

ልጅ፡የምሰራች፡እስኪ፡እባክህ፡ወር
ስልኝ፤ ከወይዘሮ፡ውቤ፡ጋር፡ትገናኛችሁ፡
ወይስ፡ሳትገናኙ፡ቀራችሁ።

ልጅ፡ዩስታ፡ቆይ፡እኮ፡ልትቸኩል፡
በሰፊው፡ሳጣውትህ፡ሦስት፡ቀን፡ከዚያው፡
ከጠረፉ፡ካደርሁ፡በኋላ፡እንዴት፡መርከብ፡
መጣች።

እኔም፡ቆሎ፡ብዬ፡እንዴት፡ጃልባ፡ይ
ዠ፡ወደ፡ስዋ፡ሔድሁና፡ከመርከቡ፡ሳይ፡ወ
ጣ፡ሁ። በፍርሃት፡ወደ፡ካፒቴኑ፡ሔጄ፡እባክ
ዎ፡ወደ፡ፓርቱ፡ስደድ፡እሔዳለሁና፡እንዴት፡





ቀራንዮ ።

የፍቅር፡ወሬ።

ክፍል፡ ይ ስጡኝ፡ብዬ፡ለመንኩት።

ካፒቴኑም፡ከላይ፡እስከ፡ታች፡ከተመለከተኝ፡በኋላ፡ላንተ፡የሚሆን፡ክፍል፡አይገኝም፡አለኝ።


እኔም፡ደንግጬ፡የፊተኛው፡የጦር፡መርከብ፡ካፒቴን፡የሰጠኝን፡ያደራ፡ወረቀት፡ረስቼው፡አግኝህ፡እዘንልኝ፡እያልኩ፡ስለምነው፡ትዝ፡አለኝና፡ወረቀቱን፡አውጥቼ፡ሰጠሁት።

እሱም፡ተቀብሎ፡ካነበበው፡በኋላ፡ለሳምንታ፡ለጥቆኝ፡ከሦስተኛው፡ማዕርግ፡እንዲት፡ክፍል፡ተረክቤ፡ዋጋውን፡ከፍዬ፡ገባሁ።

ከዚህ፡በኋላ፡መርከቡ፡ሦስት፡ሰዓት፡ያህል፡ቆየና፡ወደ፡ፓርቱ፡ሰይድ፡ተጉዞ፡ባራተኛው፡ቀን፡ደረሰ።

እኔም፡ከዚያ፡ወርጄ፡ለቀጥታ፡ካንታ





ኢየሩሳሌም፡የቅድስት፡አገር፡ከተማ።

## የፍትር፡ወሬ።

ሬ፡ ሳይ፡ በባቡር፡ ተሳፍሬ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ተጓዝሁና፡ ልክ፡ በ፲፪ ሰዓት፡ ተኩል፡ ኢየሩሳሌም፡ ደረስሁ።


ወዲያው፡ በቀጥታ፡ ወደ፡ ቀራንዮ፡ ወደ፡ መድኃኔታችን፡ መቃብር፡ ይህንን፡ተእምራት፡ ለሠራልኝ፡ አምላክ፡ ጸሎት፡ ለማድረግ፡ ሔድሁ።

ከመቃብሩ፡ መቅደስ፡ገብቼ፡ በጉልበቴ፡ ተንበርክኬ፡ ጸሎት፡ ሳደርግ፡ እንደዚሁም፡ ወይዘሮ፡ ውቤቱ፡ በዚሁ፡ ሰዓት፡ ዝወትር፡ ጸሎት፡ ስለምታደርግ፡ መጥታ፡ እኔ፡ መሆኔን፡ ሳታውቅ፡ በጉልበቷ፡ ተንበርክካ፡ ካጠገቤ፡ ጸሎት፡ ታደርግ፡ ነበር።

እኔም፡ የማንች፡ ቤት፡ ብዬ፡ ስመለከት፡ እስዋም፡ የምን፡ ሰው፡ ነው፡ ብላ፡ ስትመለከት፡ ዓይን፡ ሳይን፡ ግጥም፡ አልን።

በዚያን፡ጊዜ፡ የሁለታችንም፡ ልብ፡ በ





ጎልጎታ።


የፍቅር፡ወሬ።

ደስታና፡በትእምራት፡ምክንያት፡ደመታ፡
ጀመር።

ከዚያ፡በኋላ፡ሁለታችንም፡ከመቃብሩ፡ሳይ፡ዕንባችንን፡እያፈሰስን፡ይህንን፡ታላቅ፡ነገር፡ስላደረግህልን፡ምን፡እንከፍልህ፡ይሆን፡እያልን፡የበለጠ፡ለቅሶ፡ካደረግን፡በኋላ፡ወደ፡ጎልጎታ፡ሔደን፡ሰገድን።

ከዚያ፡በኋላ፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ፍቅሬ፡እንራችን፡ሳለን፡ባየኸው፡ሕልም፡ምክንያት፡የተሳልነውን፡ስለት፡አትርሳ፡ዛሬውኑ፡በዚሁ፡በኩል፡ወደ፡ዋርዳዊስ፡እንሒድ፡ብላኝ፡እኔም፡በዚሁ፡ተስማምቼ፡አንድ፡ታክሲ፡ይዘን፡ወርደን፡መጀመሪያ፡ጌቴሴማኒ፡ከመቤታችን፡መቃብር፡ውስጥ፡ገብተን፡ጸሎት፡ካደረግን፡በኋላ፡ወደ፡ዋርዳዊስ፡ወርደን፡ከቤተ፡ክርስቲያኑ፡አጠገብ፡ለመነኮሳት፡ከተሠራው፡ቤት፡ውስጥ፡አደርን።





ጌቴሴማኒ፡የመቤታችን፡መቃብር።

በማግስቱም፡እኔ፡ደብረ፡ሊባኖስ፡ካያቴ፡ቤት፡የማውቃቸው፡አንድ፡መነኵሴ፡በምናኔ፡ምክንያት፡አገራቸውን፡ጥለው፡ከዋርደዋስ፡በረሃ፡ብቻቸውን፡መኖራቸውን፡አውቅ፡ነበርና፡የኔ፡ፍትር፡አንድ፡የበቁ፡መነኵሴ፡ከዚህ፡በረሃ፡ይገኛሉና፡ምክር፡እንዲሰጡን፡እንሒድና፡እንያቸው፡አልኋት፡

እስዋም፡በጣም፡ደስ፡ይለኛል፡ብላ፡አንድ፡መነኵሴ፡መሪ፡ይዘን፡ሔድን።

ያሉበትም፡ቦታ፡በጣም፡አደገኛ፡ዘንዶና፡አባ፡ጊንጥ፡የመሳሰሉ፡ስለሆነ፡የሚመሩን፡መነኵሴ፡እንደንድ፡ዱላ፡ሰጥተውን፡መነኵሴው፡ከፊት፡ወይዘሮ፡ውቤ፡ከመካከል፡እኔ፡ከወደ፡ኋላ፡ሆነን፡በፍርሃት፡እየተንሳመጥንደረስን።

የመነኵሴውም፡ቤት፡ካንድ፡የሚያስፈራ፡ሸለቆ፡ውስጥ፡ዙሪያውን፡በመቃ፡የተከ





በበ፡የሚያስፈራ፡ደን፡ነው።

በድንገት፡ከመቃው፡በታች፡አንድ፡የሚያስፈራ፡ዘንዶ፡እኛን፡በማየቱ፡እየተሳበ፡ወደ፡ቍልቍል፡ዱኑን፡እያማታ፡ወረደ።

በዚያን፡ጊዜ፡ወይዘሮ፡ውቤ፡በፍርሃት፡በጣም፡ወኰች።

መነኵሴውም፡የፍርሃት፡ውኸት፡በሰሙ፡ጊዜ፡ደንግጠው፡መስቀላቸውን፡ይዘው፡ብቅ፡አሉ።

እኛም፡እሳቸውም፡በመንገድም፡እንተያይ፡ጀመር። ምክንያቱም፡መነኵሴው፡በጎርመት፡ምክንያት፡ከስተው፡ዓፅም፡መስለው፡ስለነበረ፡የማውቃቸው፡መነኵሴ፡አይደሉ፡ይሆን፡በማለት፡ተጠራጠርኩ።

ነገር፡ግን፡መነኵሴው፡ምንም፡ብከሳ፡መልኩ፡በጣም፡አልተለወጠም፡ነበርና፡እኔ፡መሆኔን፡አወቁና፡ልጄ፡ደስታ፡ተሰማ፡አ

ይዟልሁም፡ብለው፡አትፍ፡አድርገው፡ሰሙኙ።

ከዚህ፡በኋላ፡ወይዘሮ፡ውቤቱን፡የኔ፡ፍትር፡ናት፡ብለው፡አስተዋወቋት።

መነኩሲውም፡ሳቅ፡ብለው፡ፍትር፡ምን፡መሆኑን፡በመንፈስ፡አውቃችሁታል፡ን፡ወይስ፡በጠራር፡ብቻ፡ነው፡ኑ፡እንባባና፡እንጫወት፡ብለው፡ካንዲት፡ደን፡ውስጥ፡ይዘውን፡ገቡና፡ካንዲት፡ጉርማጅ፡ግንድ፡ሳይ፡ተቀመጡ፡አሉን። እኛም፡ተቀመጥን።

ከዚህ፡በኋላ፡መነኩሲው፡ይኸውላችሁ፡ጥናው፡እንግዲ፡መቀበያው፡አዳራሽ፡ካሉ፡በኋላ፡እንዲት፡ኪሻ፡የተነጠፈች፡በታ፡በጣታቸው፡እያመለከቱ፡ይህ፡መኝታ፡ቤቴ፡ነው፡ብለው፡ካሳዩን፡በኋላ፡ኪሻውን፡እንሥተው፡ጥና፡የመጥሪያ፡ቤት፡መንግሥቴ፡ይህ፡ነው፡ብለው፡አሳዩን።





እኛም፡ብድግ፡ብለን፡ብንመለከት፡መቃብራቸውን፡ምሰው፡በሳዋ፡ሳይ፡ዕንጨት፡ደርድረው፡እንድ፡ኪሻ፡አንጥፈው፡ያተኙበት፡ጥርዋል። በዚያን፡ጊዜ፡ወይዘሮ፡ውቤቱ፡ዕንባዋ፡ይፈስ፡ጀመር።

መነኩሴውም፡ምነው፡ልጄዋ፡ታለቅሽለሺ፡ይህ፡ቤት፡መንግሥት፡ለንጉሥም፡ለድሀም፡ለጻድቅና፡ለኃጥእም፡ቢሆን፡ቅርፁም፡እርዝማኔውም፡ጐኑም፡አንድ፡ነው።

የሰውንም፡ልጅ፡አንድ፡የሚያደርግው፡ይህ፡የምታዩው፡ቤት፡መንግሥት፡ብቻ፡ነው፡ብለው፡ቤት፡መንግሥቴን፡እስክነግሥ፡ድረስ፡ልዝጋው፡ብለው፡ኪሻውን፡አለበሱትና፡ከሳዋ፡ሳይ፡ተቀምጠው፡ልጆቼ፡የመጣችሁ፡በትጉዳይ፡ምንድነው፡አሉን።

እኛም፡ከግንዱ፡ጉርማጅ፡ሳይ፡ተቀ

ምጠን፡የደረሰብኝን፡ታሪክ፡ሁሉ፡ዘርዝሬን፡
አጫወትኋቸው።

ልጅ፡የምስራች፡ወይ፡ግሩም፡እንደ
ገድ፡ጊዜ፡መዓት፡ምሕረት፡ይሆናል፡እንደ
ተባለው፡ከፍ፡ያለ፡ደዊ፡አሞህ፡ስንጨነቅ፡
ለካ፡ከፍ፡ያለውን፡የእግዚአብሔርን፡ጸጋ፡ለ
ማየት፡ኖርዋል፡የተኛኸው፡እባክህ፡ወንድ
ሜ፡እስኪ፡ጨርስልኝ።

ልጅ፡ዴስታ፡ወንድሜ፡ሆይ፡በውነት፡
እንደየሁት፡አድርጌ፡ላጫውትህ፡አልችል
ም። ምክንያቱም፡የመንኩሴውን፡የመንፈ
ስ፡ብርታት፡የርቀታቸውንና፡የመኖሪያቸ
ውን፡ግርማ፡በዓይን፡ካዩት፡በወሬ፡ብቻ፡
መንፈሱ፡አይታወቅም።

የሆነ፡ሆኖ፡ጫወታችንን፡ልጨርስልህ።

ከዚህ፡በኋላ፡ልጆቼ፡ሆይ፡አጀማመሬ
ችሁ፡በጣም፡መጥፎ፡ኖርዋል፡ብለው፡ሴጀ





ምሩ፡ወይዘሮ፡ውቢቱ፡አዎን፡በጣም፡መጥ
ፎ፡ነው። ነገር፡ግን፡ካቀማችኝ፡በላይ፡የሆነ፡
ፍቅር፡ስለገጠመኝ፡ለመተው፡አልቻልኩም፡
ብሎ፡የመረረ፡ሰንግ፡አለቀሰች።

በዚያን፡ጊዜ፡መነኩሴው፡ልጂዋ፡አ
ታልቅሺ፡እግዚአብሔር፡በወደጁ፡በደዊ
ት፡አድሮ፡እግዚአብሔር፡ኃጢአትን፡ያልቆ
ጠረበት፡ሰው፡ምስጉን፡ነው፡ብሏል።

ስለዚህ፡እንደጫወታችሁኝ፡ከዚያ፡
ሁሉ፡መከራ፡አውጥቶ፡ከቅድስት፡አገር፡ያ
ደረሳችሁ፡የፍቅራችሁን፡ኃይል፡ገምቶ፡መ
ሆኑ፡አይጠረጠርም።

ልጁ፡ዴስታ፡እንተስ፡ምን፡ይሰማሃል፡
አሉኝ። አባቴ፡ሆይ፡እኔ፡እንድ፡ሽክሙ፡እን
ዴ፡ከበደው፡እንስሳ፡የምቅጠር፡ነኝ።

ምክንያቱም፡ወዲኋላዬ፡የተውኳ
ችው፡ቤት፡ስዎቼ፡ኃዘንና፡ወዲሬቴ፡የያዝኩ

የፍቅር፡ውሬ።

ት፡ካቅሜ፡በላይ፡የሆነ፡ፍቅር፡እንጻን
ድ፡ተሌቅ፡ሽክሙ፡ሆኖብኝ፡እወነቃለሁ።

ይልቁንም፡አገሬ፡የቡኤሌ፡ዜቡሌ፡
አገር፡ስትሆን፡እኔ፡በአርበኝነቱ፡ከመሬቱ፡
ላይ፡በክብር፡ባለመውደቄ፡ልብሴን፡ተገ
ፍፌ፡ራቁቴን፡የሆንሁ፡እየመሰለኝ፡ሰው፡
ባየሁ፡ቁጥር፡እፈራለሁ።

ያገኘኝ፡ሰው፡ሁሉ፡ይደበድበኝ፡ይመ
ስለኛል፡እልኳችው።

መንኩሴውም፡ሰንባቸውን፡እያፈስ
ሱ፡ልጄ፡ሆይ፡ሳገርህ፡ሰትል፡በጦር፡ሜዳ፡
ላይ፡ውለህ፡በመስደድህ፡ራቁትህን፡መሆ
ንህ፡ስለተሰማህ፡አፈርህ።

ነገር፡ግን፡የዓለም፡መድኀኒት፡ስለ፡ሰ
ዎች፡ልጆች፡ሲል፡ያለ፡አንድ፡በደል፡ያለ፡እን
ዴት፡ኃጢአት፡ራቁቱን፡በዕንጨት፡ላይ፡ሲሰ
ቀል፡ምንም፡አላፈረም።





ዮርዳኖስ ።

እንትን፡የያዘህ፡በሽታ፡የምጓጓርና፡የሃይማኖት፡መጉደሌ፡ሳይሆን፡አይቀርምና፡ዮርዳኖስ፡ሒዳችሁ፡ስትጠመቁ፡ትድናለህ። አሁንም፡ኑ፡ተከተሉኝ፡ብለው፡ወደ፡ዮርዳኖስ፡ይዘውን፡ሔዱ።

ወዲያው፡እንደ፡ደረስን፡እንዲ፡መነኩሴ፡ጠርተው፡ልብሳችንን፡አስወልቀው፡በዮርዳኖስ፡ውሀ፡እንዲያጥበው፡ሰጡት።

እኛም፡ከዮርዳኖስ፡ባሕር፡ገብተን፡እንዷ፡ጠብ፡፳መር።

በዚያን፡ጊዜ፡መነኩሴው፡በሁለታችንም፡ራስ፡ላይ፡እጁን፡ጭነው፡ጥለው፡አቡቱ፡እንደ፡ይቅርታህ፡ብዛት፡ይቅር፡በሳችው።እንደ፡ቸርነትህም፡ብዛት፡ኃጢአታቸውን፡ደምስስሳቸው፡እያሉ፡ሲጸልዩ፡እንሬችን፡ሳለን፡ያዩሁት፡ሕልም፡ትዝ፡ብሎኝ፡ስንባዑ፡እንደ፡ውሀ፡ይፈስ፡፲መር።





ከዚህ፡በኋላ፡የተጠራተመው፡የኃጢአት፡እድፍ፡እንደ፡ሟታ፡እየተቀረፈ፡ወደቀ።

በውነትም፡ከብዶኝ፡የነበረ፡ሸክም፡ከጀርባዬ፡ላይ፡እንደወረደልኝ፡ተሰማኝ። ሁለታችንም፡ከዮርዳኖስ፡ባሕር፡ስንወጣ፡ደስ፡ብሎን፡ተሎን፡ወጣን።

ወዲያው፡መነኩሴው፡ልብሳችንን፡ወተት፡አስመስሎ፡አጥቦ፡ለምጥቶ፡አለበሰንና፡ከቤተ፡ክርስቲያኑ፡ተያይዘ፡ከተሠራው፡የመነኮሳት፡ቤት፡ውስጥ፡አግብቶን፡እንደዚህ፡አለን። ከዚህ፡እድራችሁ፡ሌሊት፡በ፲ሰዓት፡አሑድ፡ከቤተ፡ክርስቲያን፡ትገባላችሁ። ወዲያውም፡አግዚአብሔር፡ከዚህ፡ካደረሳችሁ፡ኃይልና፡በርታት፡የሚሆናችሁን፡ቅዱስ፡ቁርባን፡ትቀበሳላችሁና፡ምንም፡ምግብ፡አንዳትመገቡ፡ብሎን፡ሔደ።

## ፱ምዕራፍ።

ከዚህ፡በኋላ፡ሁላችንም፡ቲሜ፡ብለን፡ያሰፈውን፡ታሪክ፡ለማወቅ፡ከሌሊቱ፡በ፯ሰዓት፡ደወሉ፡ተደወለ። ወዲያው፡ልብሳችንን፡ለብሰን፡ከቤተ፡ክርስቲያን፡ገብተን፡ሰገድን።

ወንድሜ፡የምስራች፡በዚያን፡ጊዜ፡ካህናቱ፡ልብሰ፡ተክህኖችውን፡ለብሰው፡ከመንበሩ፡ላይ፡ፃሕሉን፡ጽዋውን፡ተሰናድቶ፡ተቀምጦ፡ከማይጠገብ፡ልብ፡ከሚያሸብር፡የሻማ፡መብራት፡ከዕጣኑ፡መዓዛ፡ጋር፡ሁሉም፡ባንድነት፡ተባብረው፡ሲታዩ፡የማይታወቅ፡የደስታ፡የኃዘን፡ዕንባ፡እንደ፡ጐርፍ፡ይፈስ፡ነበር።

እኔና፡ወይዘሮ፡ውቢቱም፡ግንቡን፡ተጠግተን፡በፍርሃት፡እየተንቀጠቀጥን፡ስናለቅስ፡ቅዳሴ፡ተ፫መረ።





ከዚህ፡በኋላ፡ወደ፡መጨረሻው፡ላይ፡ዲያቆኑ፡ነጭር፡ብሎ፡በግዕዝ፡ቋንቋ፡ሲያዜም፡ቄሱ፡ቅድሳት፡ለቅዱሳን፡ብሎ፡ሲመልስ፡ኃጢአቴ፡ሁሉ፡ትዝ፡አለኝና፡እኔ፡የረከስሁ፡ሰው፡ቅዱስ፡ነኝ፡ብዬ፡በጸጋው፡ዙፋን፡ፊት፡ለቅርብ፡ነውን፡ብዬ፡ወደ፡ውጭ፡ለመሸሽ፡ስሞክር፡ለካ፡እኛ፡መነኩሴ፡ካጠገቤ፡ቆመው፡ልብሴን፡ይዘው፡ወዴት፡ትሄዳለህ፡አንተ፡ሃይማኖትህ፡የጐደለ፡እሳነበብከምን፡ማንም፡ወደኔ፡የመጣውን፡ወደ፡ሚደ፡አልሰደውም፡ያለውን፤ከዚህም፡ይበልጥ፡ወደኔ፡ኑ፡እናንተ፡ደካሞች፡ሸክማችሁ፡የከበዳችሁ፡እኔ፡አሳርፋችኋለሁ፡ያለውን፡አረሳኸው፡ብለው፡አቆሙኝና፡የጠለቀ፡ጸሎት፡አደርጋ፡ጀመር።

ጸሎቱም፡ይህ፡ነው፡ ኢቡቱ፡የዓለም፡መድኃኒት፡አንተው፡ራስህ፡ከዘጠና፡ዘጠኙ፡

በግ፡ይልቅ፡ሳንዱቁ፡ለጠፋች፡በጎ፡እንደምታዝንና፡እንደምትፈልጋት፡ባገኘሁም፡ጊዜ፡በትከሻህ፡እንደምትሸከማት፡ነግረኸኛል።

አቤቱ፡እኔ፡ኃጢአተኛ፡ሰው፡አንተ፡ወደቀራንዮ፡ተሸክመኸው፡ከሔድከው፡ከባድ፡መስቀል፡ይልቅ፡እኔ፡ላንተ፡ከባድ፡ሸክም፡ነኝ።

አንተ፡ግን፡ከትከሻህ፡ላይ፡አድርገህ፡ጠፍቼ፡በመገኘቴ፡ከፍ፡ያለ፡ደስታ፡ታደርጋለህ።

ስለዚህ——ትዱሱን፡ለመቀበል፡ተራቅዋልኛለህን።

ካደፍዋ፡ሳትነጻ፡ልብስህን፡እንደነካችው፡ሴትና፡በትዱሳት፡መማዎችህ፡ላይ፡ወድቃ፡እንዳለቀሰችው፡ዘማዊት፡ሴት፡ልትረብህን።





ሰማይ፡ስንኳን፡በፊትህ፡ንጹሕ፡ሳይሆን፡እኔ፡እንደምን፡ንጹሕ፡ነኝ፡ብዬ፡ያንትን፡ንጹሕና፡ቅዱስ፡የሆነ፡ሥጋህንና፡ደምህን፡ለሳተፍ፡እያልኹ፡ሳለቅስ፡ቄሱ፡እንደቸርነትህ፡ነው፡እንጂ፡እንደ፡ኃጢአታችን፡አይደለም፡እያለ፡በግዕዝ፡ቋንቋ፡ሲያዜም፡ሰምቼ፡ጥቂት፡ተጽናናሁና፡አቤቱ፡ያንተን፡ቅድስናና፡የኔን፡ኃጢአት፡ሳስብ፡እፍረት፡ፊቴን፡ይሸፍነኛል።

በመልክህ፡ፈጥረኸኝ፡ነበር።እኔግን፡መልኬን፡አበላሸሁት።

አቤቱ፡አንተ፡አውቀትህን፡አብርተህልኝ፡ነበር። እኔ፡ግን፡በብርሃንህ፡ውስጥ፡መሔድን፡ጠላሁ።

የጊዜው፡ለሚሆን፡ጥቅም፡በጣም፡ተጋሁ።ለማያልፈው፡ለልጅህ፡መንግሥት፡ግን፡በጣም፡ሰነፍሁ።

አቤቱ፡ኃጢአቴ፡ከራሴ፡ላይ፡ወጥቶ፡እንደንድ፡ከባድ፡ሸክም፡አስጨነቀኝ።

መምህሬ፡ሆይ፡ባለጤኖች፡መድኃኒትን፡አያሹም፡ብለህ፡ተናግረሃልና፡እኔ፡በኃጢአት፡የታመምሁ፡ድውይ፡ወዩ፡ጸጋህ፡ዙፋን፡በመቅረቤ፡ድፍረት፡አታድርጋብኝ፡እያልኩ፡ስጸልይ፡ድርገት፡ወረዱ።

እኔም፡ወይዘሮ፡ውቤቱም፡ቅዱስ፡ቅዱስ፡ቅዱስ፡ብለን፡ከመሬት፡ላይ፡ከወደቅን፡በኋላ፡ተነሥተን፡ከጸጋው፡ዙፋን፡ፊት፡ቀረብን።

ቄሱም፡የአምላካችን፡የአማኑኤል፡ሥጋ፡ነው፡ብሎ፡አቀበለን።

ወዲያው፡ደሙን፡በዕርፌ፡መስቀል፡ሲሰጠኝ፡ስለ፡ዓለም፡መድኃኒት፡ያፈሰሰውን፡ደሙን፡በጽዋው፡ውስጥ፡አይቼ፡ዕንባዬ፡ሲፈስ፡ከደሙ፡ጋር፡ተቀላቀለ።





ወንድሜ፡የምስራች፡ሆይ፡የመድኃኒታችንን፡ቅዱስ፡ሥጋና፡ደሙም፡ከተቀበልን፡በኋላ፡ኃይሉ፡በረታ። ደም፡ጣባቴም፡ተመለሰ። ፍራት፡ፍራት፡የሚለኝም፡ሁሉ፡ለቀቀኝ።

ከዚህ፡በኋላ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ወጥተን፡ማታውኑ፡የጎብቻችንን፡በዓል፡ከንጉሥ፡ዳዊት፡ሆቴል፡አከበርን።

ከዚያም፡ብዙ፡የእንግሊዝ፡መኮንኖችና፡የይሁዲና፡የዓረብ፡ሀብታሞች፡ተሰብስበው፡ይበሉ፡ይጠጡ፡ይዘፍኑ፡ነበር።

አገራችን፡ላይ፡መጀመሪያ፡የተገናኘንበትን፡ቫልሳ፡ኢምፔርያል፡በሚባለው፡የሙዚቃ፡ስልት፡ዳንስ፡ሲያደርጉ፡እኛም፡አብረን፡ተቀላቀለን፡ዳንስ፡እናደርግ፡ነበር።

ከመጨረሻውም፡ፍቅሬን፡ወደዚ

ሮ፡ ውቤቱን፡ አቅሬ፡ ለከማች፡ የቱ ሰበሰበ ው፡ ሕዝብ፡ሁሉ፡ ጽድቅና፡ ሰላም፡ተሳለሙ፡ ብለው፡ አንድነት፡ ሲያወብሙ ቡ፡ እንደ፡ መ ጠንጀ፡ ተኩስ፡ ሲወህብኝ፡ብኝን፡ አልኩ። ሕመሚያም፡ ለቀቀኝ።

ሌጅ፡የምስራች፡ እንደምን፡ የሚገ ርም፡ነገር፡ነው። ከዚህ፡በኋላ፡ እንደምን፡ሆ ንኩ።

የትወደድህ፡ወንድሜ፡ሆይ፡ብንገ ካልኩ፡ በኋላ፡ ለማይገ፡ምድር፡ዘረብኝ። ያለሁበትን፡በታ፡ ወዴት፡ እንደሆነ፡ ለማ ወቅ፡ አልቻልኩም።

መጀመሪያ፡የገባሁት፡ሆቴል፡ ሳቧ ይ፡ ስለነበረ፡ እንዳገድ፡ የማስታውሰውን፡ ዕቃ፡ብመለከት፡ አጣሁት። ወዴት፡ነው፡ያ ለሁት፡ እያልኩ፡ ሳስብ፡ ዴጋሙ፡ እንደሬትኛ ው፡ በዕንትልፍ፡ ለመመን፡ ለጥሜ፡ በነፉስ፡





ክንፍ፡ በአየር፡ እየበረርሁ፡ ወደ፡ አንድ፡ ተራራ፡ ከሆነች፡ አገር፡ ደረስሁ።

በዚያችም፡ አገር፡ ሳይ፡ ቡብዙ፡ ሺህ፡ የሚቆጠሩ፡ የቡኢሌ፡ዜቡል፡ የጦር፡መሣ ሪያዎች፡ በየሽለቆው፡ በየሚዳው፡ በየሸ ንተረሩ፡ ወድቀው፡ አየሁ።

ከዚህ፡በኋላ፡ከተራራው፡ማፍ፡በቡ ኢሌ፡ዜቡል፡ ጦርነት፡ጊዜ፡ በጦር፡ሜዳ፡ሳ ይ፡ ስያፉን፡መዞ፡ አርበኞቹን፡ አገራችሁ ንና፡ንጉሣችሁን፡ጥሳችሁ፡ ወዴት፡ትሔ ዳላችሁ፡ እያለ፡ከሚያስጋው፡ ጦር፡ሜዳ፡ ሳይ፡ የነበረው፡ንጉሥ፡ካዩጋው፡ ድኖ፡ከን ግሥቲቱ፡ጋር፡ በዙፋኑ፡ ሳይ፡ በክብር፡ተ ቀምጦ፡ግራና፡ቀኝ፡ ሕዝቡ፡ተሰብስቦ፡እ ኒና፡ ወደዚሮ፡ ውቤቱ፡ ከዚያው፡ካጠገቡ፡ ወረድን።

ወዲያው፡ንጉሡ፡ እጁን፡ ዘርግቶ፡

በፍቅር፡ተቀብሎኝ፡ለኔም፡የሥልጣን፡በትርና፡የክብር፡ልሻን፡ሸልሞ፡ጉንጩን፡ጉንጩን፡ሳመኝ።

እንደዚሁ፡ወይዘሮ፡ውቢቱንም፡የክብር፡አክሊል፡በራስዋ፡ላይ፡ደፍቶ፡የክብር፡ልሻን፡ሸልሞ፡ጉንጯና፡ጉንጯን፡ስሞ፡እኔ፡በንጉሡ፡አጠገብ፡እስዋም፡በንግሥቲቱ፡አጠገብ፡ተቀመጥን።

ወንድሜ፡የምስራች፡በደስታችን፡ውስጥ፡በጣም፡አዋንት፡የሚሰብር፡ኀዘን፡ያዘንኩት፡ግራና፡ቀኝ፡የቆሙት፡ሕዝቦች፡በቀኝ፡የቆሙት፡ግርማቸው፡የሚያስፈራ፡ጠጉራቸው፡የአንበሳ፡ጋማ፡የመሰለ፡ኃያላን፡ሰዎች፡ነበሩ።በግራ፡የቆሙት፡የደነገጡ፡ነበሩ።ይልቁንም፡እንዳንዶቹ፡የብኤልዜቡል፡ምልክት፡በግንባራቸው፡ላይ፡ስለተጻፈ፡እሱን፡ለማጥፋት፡በመሐረባቸው፡አ





የጠረጉ፡እንዲዶታዎ፡ሲሸሸጉ፡ስላየሁ፡በጣም፡አዘንሁ።

ከዚህ፡በኋላ፡በጣም፡ጥልቅ፡በሆነ፡ዝምታ፡ሕዝቡ፡ሁሉ፡እኛን፡እየተመለከተ፡የእግዚአብሔርን፡ታምራት፡ሲያደንቁ፡መድፍ፡ተተኰሰ።

በዚያን፡ጊዜ፡በመድፉ፡ድምፅ፡ብንን፡አልኩ።

ከዚህ፡በኋላ፡አእምሮዬ፡ተመልሶ፡ያለሁበትን፡ቦታ፡አወቅሁት።

ይኸውልህ፡ወንድሜ፡እንደዚህ፡ያለ፡የሚገርም፡ነገር፡ነው፡ያየሁት፡አለው።

ልጅ፡የምስራችም፡በጣም፡የሚያስደንቅ፡ታሪካዊ፡ቅዠት፡ነው።

አደራህን፡ወዳጄ፡እንዳይረሳህ፡ደፍና፡አስቀምጠው፡ብሎት፡ፕሪስ፡ላይ፡ብዙ፡ሥራ፡ካለበት፡ወደ፡ሌጋሲዮኑ፡ተመ

ለስ ።—

## ፲ ምዕራፍ።

የዚህ፡ የልብ፡ ወለድ፡ መጽሐፍ፡ መነሻ፡ የሆነው፡ ልጅ፡ ደስታ፡ተሰማ፡ ለኔ፡ ጥና፡ እንደ፡ነፍሴ፡የማፈቅረው፡ከፍ፡ባለ፡ ግምት፡የምገምተው፡ወዳጄ፡ነው።—

ራሱ፡መልኩና፡ ደም፡ግባቱ፡ሲያዩት፡ ፍቅር፡ማለት፡እሱው፡ነው።—

ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡ ማንንም፡ ሰው፡ ሬቱን፡ አጥቂሮ፡ አይቀበልም። ማንም፡ሰው፡ ጠላቱም፡ቢሆን፡ ቢወነትና፡መንራሱ፡ ቢታወክ፡ አይወድም።—

በጣም፡ ስለምወደው፡ የሰውየው፡ ሥዕል፡ከሬቱ፡በመንፈስ፡ ስለሚታየኝ፡ ብልህ፡ የሆንህ፡ አንባቢ፡ በምሰጥህ፡ምልክቶች፡ ልትሥለው፡ትችላለህ።—





ልጅ፡ ደስታ፡ተሰማ፡ ቁመቱ፡ ረጅም፡ ደረቱ፡ሰፊ፡ሥጋውና፡ አጥንቱ፡ በመልካም፡ የተገነቡ፡ናቸው።—

ጠጉሩ፡ሐር፡የመሰለ፡ጥቁር፡ከርዳዳ፡ ግንባሩ፡ እንደ፡ ቁመቱ፡ መጠን፡ በልክ፡ የተሠራ፡ ነው።—

ነገር፡ግን፡ግራና፡ቀኝ፡ እንደ፡በሬ፡ ጠጉሮቹን፡ገልጠው፡ገብተዋል።—

ሽፋሉ፡ ሐር፡ መስሎ፡በብዙ፡በቅሎ፡ ከግንባሩ፡በታች፡ግጥሞ፡ሳይኑ፡ ዋናጊዋ፡ ሆኖ፡ይታያል።—

ቅንድቦቹ፡ በርከት፡ብለው፡ በቅለው፡ ሳይኑ፡ ጠባቂ፡ዘበኛ፡ የቆሙ፡ መስለው፡ይታያሉ።—

ዓይኖቹ፡ ልከኛ፡ ሆነው፡ በጣም፡የሚያምሩ፡ናቸው።—

አፍንጫው፡ሰልካካ፡በጣም፡የሚያ

ምር፡ይህ፡ቀረው፡የማይባል፡ነው።

ከንፈሩ፡በሰውነቱ፡መጠን፡የተሠራና፡የታችኛው፡ከንፈሩ፡ጥቂት፡ዘርጋ፡ያለው፡ነው።

ጢሙ፡ዘወትር፡ስለሚላጭ፡አይታወቅም። ነገር፡ግን፡ሪዙ፡በጣም፡ያነሰ፡ነው።

ጥርሶቹ፡የተካከሉና፡የሚያምሩናቸው። ከላይኛው፡ጥርሶቹ፡ላይ፡ፊት፡ለፊት፡ከሚታዩት፡ከሁለቱ፡ጥርሶቹ፡ላይ፡ነጫጭ፡ልዩ፡ቀለሞች፡አሉበት።

ይህንንም፡የሚወዱት፡ሰዎች፡የሰፍሬ፡ኮከብ፡ነው፡ይሉ፡ነበር።

አንገቱ፡ልክ፡በሰውነቱ፡መጠን፡የተሠራ፡ነው።

እንደዚሁም፡ደረቱ፡እንደ፡ሰውነቱ፡የተመጠነ፡ነው።

የእጆቹ፡ጣቶች፡በጣም፡ረቂቅ፡አይ





ዲሉም። በጠቅላላው፡ልጅ፡ዲስታ፡ተሰማ፡የወይን፡ሐረግ፡የመሰለ፡መልክ፡መልካም፡ወጣት፡ነው። ጥቂት፡እግሩ፡ትልቅ፡ነው።

ከዚህ፡ቀጥሎ፡አብሬው፡ስለኖርኩ፡ከብዙው፡በጥቂቱ፡ጠባዩን፡ለማስረዳት፡እችላለሁ።

፩ኛ፡ልጅ፡ዲስታ፡ተሰማ፡ማንኛውም፡ሰው፡ይወዳል።

ነገር፡ግን፡ባልንጀራ፡የሚያደርገውን፡ሰው፡በጥንቃቄ፡ይመርጣል። ይልቁንም፡የውነተኛ፡ባልንጀራ፡ለማድረግ፡በብዙ፡መላመድን፡ይጠይቃል።

ምክንያቱም፡ከወደደ፡ወዲያ፡ለዚታም፡ቢሆን፡አይርኀ፡መጥላትና፡ወረት፡የለውም።

፪ኛ፡በራሱም፡ቢሆን፡በልጆቹ፡ችግ

ር፡እንዲያደርስበት፡በብልጠቱና፡በው
ቀቱ፡ገንዘብ፡ሳከማች፡ብዙ፡ርስት፡ሊሰ
ብሰብ፡አይልም።

ምክንያቱም፡ገንዘብና፡መሬት፡ለ
ባለ፡ርስቱ፡የማይደፈር፡በሕግ፡የተጠበቀ፡
ርስቱ፡ነው፡የሚባለውን፡ቷንቷ፡የማያም
ንበት፡ስለሆነ፡ነው።

ይህንን፡የሥጋ፡ማኅበር፡ያልታመነ፡
የሰው፡ልጆች፡መብት፡ጊዜ፡እንደ፡ሸረው፡
እንደ፡በታትነው፡ሰለሚያውቅ።

ከቅዱስ፡ዳዊት፡ጋር፡ያከማቻሉ፡ለ
ማን፡እንደሚሰጡት፡አያውቁም፡አያለ፡
ያዝናል።

፫ኛ፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡የራሱን፡የ
ግል፡ደስታ፡በጣም፡ይወዳል፡ በወጣትነቱ፡
ዘመን፡እሱ፡ያልቀመሰው፡ደስታ፡አይገኝም፡
ባገሩ፡ሳይ፡ብቻ፡ሳይሆን፡በዙ፡ባለማትን፡እ





ይትዋል። ለምሳሌ፡ሮማን፡አሜሪካን፡እና
ሬካን፡እዝያን፡ከብዙው፡በጥቂቱ፡ኀብኝት
ጥል። በነዚህም፡ውስጥ፡ከሩው፡ንም፡ደግ
ንም፡ደስታዎች፡ተምሰዋል።

ነገር፡ግን፡ስሎሞን፡የተሠወረ፡ኃጢ
አት፡የንስሐ፡ግማሽ፡ነው፡እንዳለው፡ ልጅ፡
ደስታ፡ተሰማ፡የግል፡ደስታውን፡በመመደ
ደት፡መጋረጃ፡ሰለሸፈነው፡በወገኖቹ፡ዘ
ንድ፡እንደንድ፡ቅዱስ፡ይቆጠር፡ነበር።

የልጅ፡ደስታ፡ዋና፡ጠባዩ፡እንደ፡ቅዱ
ስ፡ጳውሎስ፡እሽከር፡እንደ፡ዴማስ ፡ ከብ
ር፡ጉድጓድ፡ውስጥ፡ወድቆ፡መሠበርን፡እ
ንደንድ፡ኃጢአት፡ይቆጥረዋል።

ነገር፡ግን፡የማሰረግን፡ተራራ፡ተፍ
ወርዋሮ፡ከጫፉ፡ሳይ፡መውጣትን፡ይወ
ዳል።

፬ኛ፡ለውሀ፡መስጠት፡ለእግዚአብሔ

ር፡ማበጀር፡ነው፡የተባለውን፡ምሳሌ፡በ
መከተል፡ዘወትር፡ለድሆች፡ወገኖቹ፡
እጁን፡መዘርጋት፡ይወዳል።

መድኃኒታችን፡ተኝ፡እጅህ፡የሚሰጠ
ውን፡ግራ፡እጅህ፡አይየው፡ያለውን፡የበጐ፡
ሥራህ፡ዕንቅፋት፡እንዳይሆኑህ፡ሚስትህ
ንና፡እሽከሮችህን፡አታማክር፡ማለት፡ነው፡
ብሎ፡ስለተረጐመው፡ዘወትር፡ባደባባይ
ም፡በኅቡዕም፡መካከል፡የተቸገረ፡ወገድ
ሙን፡ካገኘ፡ምጽዋት፡ይሰጣል።

እንደያውም፡እንጀራህን፡በውሀ፡ላ
ይ፡ጣለው፡የተባለውን፡ምሳሌ፡በመመል
ከት፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡ልብስ፡የለበሱም፡
ራቁቱን፡ም፡የሆኑ፡የታመመም፡ያልታመ
መም፡ቢሆን፡ከለመኑት፡ለማንም፡ሰው፡
የተቻለውን፡ያህል፡ገንዘቡን፡ይሰጣል።

ምክንያቱም፡ሰው፡ካልተቸገረ፡የ





መለመኘን፡የውርደት፡በር፡ከፍቶ፡አይ
ገባም፡ነበር፡በማለት፡ነው።

፫ኛ፡በኦርቶዶክስ፡ሃይማኖቱ፡አ
ንደኛ፡ብርቱ፡የጠነከረ፡ነው። ሃይማኖት፡
ብርቱ፡ኃይል፡ነው። ሃይማኖት፡ጋሻና፡ጦ
ር፡ነው። ሃይማኖት፡ለሰው፡ልጅ፡የመል
ካም፡ሥራዎች፡መሪ፡ከፍ፡ያለ፡ብርሃን፡
ኃይል፡ነው፡ይል፡ነበር።

ለምሳሌ፡ባትሪው፡ያልተሞላ፡አ
ቶመቢል፡በመለማ፡እንደማይንቀሳቀ
ስ፡ እንደዚሁም፡ሰው፡ በሃይማኖት፡ብ
ርሃን፡ሰውነቱን፡ካልሞላ፡ዘወትር፡በቀ
ቢጸ፡ተስፋ፡ውድቅት፡ጨለማ፡ውስጥ፡
ይኖራል።

ስለዚህ፡ወደ፡መልካም፡ነገር፡የም
ንሔድበት፡ፋና፡ሃይማኖት፡ስለሆነ፡በሃ
ይማኖታችን፡ሳይ፡ምግባራችንን፡እንመ

ሥርት፡ይል፡ነበል።

፯ኛ፡የልጅ፡ደስታ፡ፈሉዘሬ፡ስለ ምንድነው፡የሰው፡ልጆች፡ባልተመዘዘኑ ኑሮ፡የሚኖሩት፡በማለት፡ያዝናል።

የሰው፡ልጅ፡ከወንድሙ፡በላይ፡በ መሆኑ፡ሰው፡መሆኑን፡ለምን፡ይረሳል። ይልቁንም፡ገንዘቡን፡ያገኘው፡በድሆች፡ ወንድሞቹ፡ወዝና፡ደም፡መሆኑን፡እያ ወቀ፡ደሙ፡ተመጦ፡ቁርበቱ፡ብቻ፡ሲቀር፡ ለምን፡ይወረውረዋል።

እነሆ፡የዕለት፡ልብስና፡የዕለት፡ጉር ስ፡አጥተው፡በቤተ፡ክርስቲያን፡ቅጥር፡ ውስጥና፡በመቃብር፡ቤት፡ወድቀው፡ይ ታያሉ። የሚበልጡትም፡መብታቸውን፡ ተነጥቀው፡የፍርድን፡የብረት፡በር፡ከፍ ተው፡ለመግባት፡የገንዘብ፡መክፈቻ፡ስ ለሌላቸው፡ፍርድ፡ፍርድ፡እያሉ፡በመንገ





ድ፡ወድቀው፡ይገኛሉ።

በዓለም፡ላይ፡ሥልጣኔ፡በመጨመ ር፡ቁጥር፡በድሆች፡ላይ፡ችግር፡እየጨመ ረ፡ይሔዳል።

ስለዚህ፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡መጀመ ሪያ፡ራስን፡መውደድና፡ጭካኔን፡ከሥራ ቸው፡ነቃቅለህ፡ጣላቸው። ከዚህ፡በኋላ፡የ ቀሩት፡ኃጢአቶች፡አውቀው፡ይደርቃሉ ይል፡ነበር።

፰ኛ፡የልጅ፡ደስታ፡ፈሉዘሬ፡እንዴ ግዲ፡ሰዎች፡ይህ፡ዓለም፡የከርታ፡መጨዋ ቻ፡ካዚኖ፡መሆኑን፡ስለተሰማቸው፡ገንዘ ባቸውን፡ለመንግሥታቸውና፡ለድሆች፡ ወንድሞቻቸው፡ሰጥተው፡የክርስቶስን፡ ዱካ፡ተከትለው፡ከዚህ፡ዓለም፡ወጥመ ድ፡ሲሸሹ፤ ሌሎች፡ደግሞ፡ለዚህ፡ኃይሉ፡ ለሚጠፋ፡ገንዘብ፡ወንድማቸውን፡በሥው

ር፡ ወይም፡ በጓልዋ፡ገድለው፡ ለመጠቀም፡
የሚጥሩ፡ ለምንድነው፤ ይህ፡የሐሳብ፡ አ
ለማመዛዘን፡ ያሳዝናል፡ይል፡ነበር።

፲ኛ፡ ልጅ፡ ዩስታ፡ተሰማ፡ እንደዚህ፡
ይል፡ነበር።

ይህ፡ዓለም፡የመነጣጠቂያና፡የክንቱ
ነት፡ገበያ፡ስለሆነ፡የሰው፡ልጅ፡በዘመኑ፡ም
ክንያት፡ ዕድሉ፡ ሲያብብ፡ በሌላው፡ዘመን፡
ደግሞ፡ዕድሉ፡ይጠወልግና፡ቤቱ፡ፈርሶ፡ር
ስቱ፡ተሸጦ፡ይታያል።

በጊዜ፡ምክንያት፡አዳኘኙ፡የነበረ፡አን
ድ፡ሰው፡ጊዜ፡ጥሎት፡ፍለጋው፡ስንኳን፡የማ
ይገኝ፡ይሆናል።

ስለዚህ፡ቅዱስ፡ዳዊት፡ኃጢአተኛው
ን፡ ሰው፡ እንደ፡ዲጋ፡ዛፍ፡ አየኹ፡ከፍ፡ከፍ፡ብ
ሎ፡ አየሁት። ብመለስ፡ግን፡ አጣሁት። ስ
ፍራውንም፡ብፈልግ፡አላገኘሁትም፡ይላል።





ስለዚህ፡በጊዜ፡መሪነት፡የሚሔድ፡የ
ሰው፡ልጅ፡ብልጠት፡የከንቱ፡ከንቱ፡በመሆ
ኑ፡ያዝን፡ነበር።

የመንጋ፡እናት፡ተንጋላ፡ትሞት፡እን
ደተባለው፡ይህ፡ዓለም፡አንድ፡እጁን፡ወደ፡ገ
ነት፡ አንድ፡እጁን፡ወደ፡ገሃነም፡ዘርግቶ፡ ይ
ታያል። ማለት፡ባንድ፡ፊት፡ብዙ፡የበጐ፡
ሥራ፡ማኅበር፡ሲዘጋጅ፡ይታያል።

ለምሳሌ፡ሆስፒታል፡እናት፡አባት፡ለሌ
ላቸው፡ልጆች፡ማሳደጊያ፡ሆስፒታልና፡የሽ
ማግሌዎች፡መጦሪያ፤ ትምህርት፡ቤት፡የድሆች፡
ልጆች፡መቀበያ፡በረት፤ ይህንን፡የመሰለ፡ብ
ዙ፡የርኅራኄ፡ሥራ፡ይሠራል።

በሌላው፡በኩል፡ደግሞ፡የሰውን፡ልጅ፡
ዘር፡የሚመትሩ፡ ቦምብ፡ አቶሚክ፡ ቦምብ፡
ሃይድሮጂን፡ ይህንን፡የመሰሉ፡የጥፋት፡ መ
ሣሪያዎች፡ሲዘጋጁ፡ይታያሉ።

ስለዚህ፡የሰው፡ልጆች፡ሥራ፡ባንድ፡ሌት፡ሲገነባ፡ባንድ፡ፊት፡የሚፈርስ፡የልጆች፡የጊዜ፡ካብ፡ነው፡ለማለት፡ያስደፍራል፡ይላል፡ነበር።

፲፫ኛ፡ ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡የሰው፡ልጅ፡ስለምንድነው፡ራሱን፡ብቻ፡የሚወድ፡ራስን፡መውደድ፡ከእግዚአብሔር፡ጋር፡ለመስማማት፡ጥልቅ፡የሆነ፡የማይዘለል፡ገደል፡እንደመማስ፡ያለ፡ነው።

መድኃኒታችን፡ለእግዚአብሔርና፡ለገንዘብ፡ልትገዙ፡አትችሉም፡ይላል፡ይህን፡ማለት፡እግዚአብሔርን፡ወይም፡ገንዘብን፡ማምለክ፡ነው፡እንጂ፡ሁለቱን፡ባንድነት፡ማምለክ፡እንደማይቻል፡ያስረዳናል፡

ለምሳሌ፡አንድ፡ሰው፡ባዲስ፡አበባ፡ከተማ፡ውስጥ፡በገንዘብ፡ፍቅር፡እንደምን፡ባለ፡አሟሟት፡እንደ፡ሞተ፡ላሳስባችሁ፡





አሬቶ ዲለሁ።

ይህ፡ሰው፡ካብቱን፡በቤቱ፡ውስጥ፡ቀብሮ፡ጠዋት፡ማታ፡ያየው፡ይመለከተው፡ነበር።

ከዕለታት፡አንድ፡ቀን፡አንዱ፡ወዳጁ፡ወንድሜ፡ሆይ፡ብዙ፡ገንዘብ፡በቤትህ፡ውስጥ፡አስቀምጠሃል፡እየተባለ፡ይወራል፡ስለዚህ፡ምናልባት፡ቤትህ፡ቢቃጠል፡ወይም፡ሌባ፡ገብቶ፡ቢዘርፍህ፡ድካምህ፡ከንቱ፡ይሆናልና፡እኔ፡የምመክርህ፡ገንዘብህን፡ሁሉ፡ከባንክ፡ብታስቀምጠው፡ይሻላል፡ብሎ፡መከረው።

ያም፡ካብታም፡ሰው፡ወንድሜ፡ሆይ፡ብዙ፡ደክሜ፡ያገኘሁትን፡ገንዘብ፡በትርቡ፡ካጠገቤ፡ያጣሁት፡እንደሆን፡ደስ፡አያለኝም። ከባንክማ፡ያስቀመጥሁት፡እንደሆን፡ጭራሽ፡የሌላ፡ሰው፡ገንዘብ፡ይመስለ

ኛል፡ አለው።

ወዲጁም፡ ሳይለይም፡ እኔን፡ ስማኝ፡ ባይሆን፡ እንኳን፡ ሳማሹን፡ ገንዘብህን፡ ከባንክ፡ አስቀምጠው።

ምክንያቱም፡ ከቤት፡ ውስጥ፡ ያለ፡ ገንዘብ፡ ቢታጠል፡ ወይም፡ ቢጠፋ፡ እንኳ፡ ከባንክ፡ ባለው፡ ገንዘብ፡ ትቋቋማለህ፤ እባክህ፡ ምክሬን፡ ስማ፡ ብሎ፡ ስለለመነው፤ ካብታሙ፡ ሰው፡ እሺ፡ ስለወዲጁነትህ፡ ምክር፡ ስላሳ፡ ሺህ፡ ብር፡ ያህል፡ ከባንክ፡ አገባለሁ፡ ብሎ፡ ሰላሳውን፡ ሺህ፡ ብር፡ ገንዘቡ፡ በዝርዝር፡ ያንዳንዱ፡ ብር፡ ስለሆነ፡ በሣስት፡ የልብስ፡ ሣጥን፡ አሽክሞ፡ ከባንክ፡ አስቀመጠ።

ከዚህ፡ በኋላ፡ የከተማ፡ ቦታ፡ በርካሽ፡ ስላገኘ፡ ከቤቱ፡ ውስጥ፡ የተቀመጠውን፡ ገንዘብ፡ ከማጉደል፡ ሰላሳ ሺህ፡ ብር፡ ከባንክ፡ አውጥቶ፡ ለመግዛት፡ ሁለት፡ ትልልቅ፡ ሣጥን፡





ከታመኑ፡ ልጆቹ፡ ጋር፡ ይዞ፡ ወደ፡ ባንክ፡ ሔደ።

ከዚያም፡ እንደ፡ ደረሰ፡ ካስቀመጠው፡ ገንዘብ ሰላሳ ሺህ፡ ብር፡ ለመውሰድ፡ እፈልጋለሁ፡ ብሎ፡ አስታወቀ።

የባንኩም፡ ዲሬክተር፡ የሚያስፈልገውን፡ ፎርማሊቴ፡ ከሸኙ፡ ሳይ፡ አስፈርሞ፡ ገንዘቡን፡ አሁው፡ ራሱ፡ በኪሱ፡ እጅርጉ፡ ለመውሰድ፡ እንደ፡ መቸው፡ ያምስት፡ ያምስት፡ መቶ፡ የገንዘብ፡ ኖት፡ ባንቦልክ፡ እጅርጉ፡ አመጣለት።

ይህ፡ ንብረትም፡ ሰው፡ እሱ፡ የለመደው፡ የዝርዝር፡ ገንዘቦች፡ ስለሆነ፡ ሣጥኑን፡ ይዞ፡ መጥቶ፡ ነበርና፡ ባንዲት፡ እንቦልክ፡ ሰላሳ፡ ሺህ፡ ብር፡ ያምስት፡ መቶ፡ ያምስት፡ መቶ፡ የኢትዮጵያ፡ ዴሳር፡ ይዞ፡ መጥቶ፡ ቢሰጠው፡ ያሸማግሌ፡ ደንግጦ፡ ይህ፡ ብቻ፡ ነውን፡ የኔ፡ ገን

ዞብ፡ እያሱ፡ ይንቀጠቀጥ፡ ጀመር።

የባንኩ፡ የሥራ፡ ክፍል፡ ሹም፡ ይኸው፡ ብቻ፡ ነው፡ ያስቀመጡት፡ ገንዘብ፡ ብሎ፡ ሲመልስለት፡ ሰውየው፡ በድንጋጤ፡ ብዙ፡ ላብ፡ አልቦት፡ እባክህ፡ ልጁ፡ እንደዚህ፡ ነው፡ የባንክ፡ ሥራ፡ ብሎ፡ ጠየቀው።

የባንኩም፡ ሠራተኛ፡ አዎን፡ እንደዚሁ፡ ነው፡ ብሎ፡ ሲመልስለት፡ ካብታሙ፡ ሰው፡ ራሱን፡ አዞሮት፡ ወደቀ።

ከዚህ፡ በኋላ፡ ልጆቹ፡ ከቤቱ፡ ወስደው፡ አስተኙትና፡ በጆሮው፡ እየቀረቡ፡ ገንዘባችን፡ አልጠፋም፤ ያው፡ ያገባነው፡ ገንዘብ፡ ነው፡ እያሉ፡ ቢነግሩት፡ በጣም፡ ስለደከመ፡ ምንም፡ አይሰማም፡ ነበር።

ብቻ፡ ሌሊቱን፡ ሁሉ፡ ስርቅ፡ ስርቅ፡ እያለው፡ አልሮ፡ አልሮ፡ ገንዘቤ፡ እያለ፡ ሲንጋጋ፡ ሞተ።





ስለዚህ፡ ልጅ፡ ዲስታ፡ትስማ፡ እንደዚህ፡ ይል፡ ነበር።

መድኃኒታችን፡ በወንጌል፡ ገንዘብ፡ የሚወድ፡ ካብታም፡ ይጸድቃል፡ ከማለት፡ ግመል፡ በመርፌ፡ ቀዳዳ፡ ይሾልካል፡ ማለት፡ ይቀላል፡ ብሎ፡ እንደተናገረው፡ ገንዘብ፡ የሚወድ፡ ሰው፡ ለማፃት፡ ሰማዕት፡ ሆኖ፡ እንደሚሞት፡ ሰው፡ ያለ፡ ስለሆነ፡ ለእግዚአብሔርም፡ ለሰውም፡ ወዳጅ፡ እንደማይሆን፡ የታወቀ፡ ነው።

፲ኛ፡ ዲስታ፡ትስማ፡ ስለ፡ ሰዎች፡ ልጆች፡ በእውቀት፡ አለመመዛዘን፡ በጣም፡ ያዝን፡ ነበር።

ምክንያቱም፡ ያንድ፡ ዛፍ፡ ፍሬዎች፡ ሲሆኑ፡ እንዱ፡ ጥበብን፡ እያፈለቀ፡ መጻሕፍቶችን፡ እየጻፈ፡ ለዓለም፡ እውቀቱን፡ ወራ፡ ያበራል። ሌላውም፡ ግን፡ በእውሬዎች፡

ትሬ፡ውስጥ፡የእውቀት፡ወሬ፡ሳያበራለ
ት፡በቀቢጸ፡ተስፋ፡ጨለማ፡ውስጥ፡ይኖ
ራሉ፡በማለት፡ይገረም፡ነበር።

፲፮ኛ፡ ልጅ፡ ደስታ፡ተሰማ፡ ለድሉ፡መ
ርጣ፡ክፍ፡ክፍ፡ያደረገችውን፡ሰው፡ማግ
ኘም፡ቢሆን፡አያከብረውም፡ነበር።

ምክንያቱም፡ ለድሉ፡ዓይን፡ሥውር፡
ስለሆነች፡ዘወትር፡የምትመርጠው፡ሳ
ታይ፡በዳሰሳ፡ስለሆነ፡በካብቴና፡በድሉ፡
አይደነቅም፡ነበር።

፲፯ኛ፡ ልጅ፡ ደስታ፡ብዙ፡የመንግሥ
ት፡ሹማምንቶች፡የመንግሥቱን፡ሥራ፡ሲ
ሠሩ፡ዘወትር፡በዝግ፡ቤት፡በቆይታ፡ጊዜያ
ቸውን፡ያጠፋሉ። ስለዚህ፡ለሕዝብ፡የ
ሚጠቅምን፡ጉዳይ፡በምሥጢር፡ጊዜን፡ማ
ጥፋት፡እንደንድ፡ኃጢአት፡እቆጥረዋለ
ሁ። ሸሻጊ፡ባይኖር፡ሌባ፡ባልተገኘም፡ነበር፡





እንደሚባለው፡የሕዝብና፡የሀገር፡ጉዳይ፡
በምሥጢር፡ባይሆን፡መንቀፍና፡ለሚታ፡
ባልተገኙም፡ነበር፡ይላል።

፲፰ኛ፡ ልጅ፡ ደስታ፡ተሰማ፡በሰው፡መ
ታመንን፡ጥና፡ኃጢአት፡ነው፡ይል፡ነበር።

ምክንያቱም፡በሞትና፡በሱብቀኛ፡የ
ሚለወጥን፡የሰው፡ባህርይ፡ስለማይታማ
መንበት፡ነው።

፲፱ኛ፡ ልጅ፡ ደስታ፡ ደጉች፡ሰዎች፡በ
ዚህ፡ዓለም፡ሳይ፡ተጠቀተው፡ክፉዎች፡ሰ
ዎች፡በዚህ፡ዓለም፡ሳይ፡ሲቀናቸው፡በማ
የቱ፡በጣም፡ይገረም፡ነበር።

አንደንድ፡ጊዜም፡ምን፡ይደረግ፡የዚ
ህ፡ዓለም፡ገገር፡ሰይጣን፡ነው፡ተብሎ፡ተጽ
ፏል።

መድኃኒታችንም፡መንግሥቱ፡ከዚህ፡
ዓለም፡አይደለችም፡ብሏል።

የፍቅር፡ወሬ።

ስለዚህ፡ልጅ፡ዲስታ፡ተሰማ፡ዓለም፡ሆዷ፡ከባድ፡ሸክም፡ሊቦችና፡ተማኞች፡የሚካፈሉሽ፡እያለ፡ያዝን፡ነበር።

፲፩ኛ፡ ልጅ፡ ዲስታ፡ተሰማ፡ምስጋና፡የሰው፡ልጆች፡እውነትንና፡ቅን፡የሆነ፡ፍርድን፡እንዲደሠሩ፡ማደንዘዝና፡እንዲተኙ፡የሚወጋ፡የእንቅልፍ፡መርፌ፡ነው፡ይል፡ነበር።

እንዲያውም፡ጉቦ፡ማማለጃ፡ከሰጡ፡ሰዎች፡ይልቅ፡በከንቱ፡ውዳሴ፡የሰውን፡እውነትና፡ቅን፡ፍርድን፡ያጠፉ፡ይበዛሉ።

ነገር፡ግን፡ሰው፡በመንፈሳዊ፡ብርቱ፡ጭንጫ፡ሳይ፡ሃይማኖቱንና፡ምግባሩን፡በ



የፍቅር፡ወሬ።

ጠንካራ፡መሠረት፡ከመሠረተ፡የዚህን፡ዓለም፡ዲስታዎች፡ይጠላል።

ስለዚህ፡የታመነ፡ዲስ፡ያለው፡ራስን፡ከመውደድ፡ባርነት፡ነፃ፡ይሆናል።

እንደዚህ፡ያለችውን፡ነፍስ፡ከመጥፎ፡ከሥጋዊ፡አሳብ፡ስለሚያነፃት፡የዚህን፡ዓለም፡ከንቱ፡ኑሮ፡ርካሽ፡እድፍ፡የእግዚአብሔር፡ጸጋ፡እንደ፡ጥሩ፡ፏፏቴ፡እጥቦ፡ያነፃለታል። እንደዚህ፡ያለው፡ሰው፡በእጁ፡የሚዳሰሱ፡ገንዘቦች፡ስለሌሉት፡በሰማይ፡ወደ፡አስቀመጠው፡ድልብ፡ሰማይ፡ሰማይ፡ይመለከታል።

ስለምን፡ማለት፡መሬታዊ፡የሆነውን፡የዚህን፡ዓለም፡እድፍ፡በጸጋው፡ፏፏቴ፡ስላጠበለት፡ነው።

፲፪ኛ፡ ልጅ፡ዲስታ፡ተሰማ፡እንዳንድ፡ጊዜ፡የሚያሳዝን፡ነገር፡ሲደርስበት፡በጣ

ም፡ አይጠነቀቅም፡ነበር።—

ምክንያቱም፡ባሳሰበው፡ነገር፡በድን
ገት፡በሚደርስበት፡መከራ፤ ካቀሜ፡በላ
ይ፡ያሳሰበው፡የደረሰብኝ፡አደጋ፡ስለሆነ፡
ምን፡ማድረግ፡ይቻላል፡በማለት፡በትዕ
ግሥት፡ይቀበለዋል።—

ነገር፡ግን፡እሱው፡ራሱ፡አውቆ፡በገ
ባበት፡መከራ፡የሆነ፡እንደሆነ፡አውቄ፡አድ
ርጊዋለሁ፡በማለት፡አያዝንም።—

፲፩ኛ፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡እንደዚህ፡
ይል፡ነበር። በብልጠትና፡በማታለል፡የተ
ከማቸ፡ገንዘብ፡ከሦስትና፡ካራት፡ትውል
ድ፡በኋላ፡ለልጆቻቸው፡የወዋ፡ልጅነትን፡
ስም፡ይሰጣቸዋል።

እንደዚሁም፡ከሁለት፡ከሦስት፡ትው
ልድ፡በኋላ፡ልጆቻቸው፡ድሆች፡ሆነው፡ሲ
ለምኑ፡ይታያሉ።—





እንደዚሁ፡ዓለም፡ሲለዋወጥ፡በክን
ቱ፡የተሰበሰበ፡ገንዘብ፡የፍዳ፡መከፋፈያ፡
ሆኖ፡ይገኛል።—

ያ፡ያዋቂው፡ልጅ፡ቲል፡የኀይለኛ
ው፡ልጅ፡ሰነፍ፡የሞኙቱ፡ልጅ፡ነዝርህር
ኸ፡ይሆናሉ። ያ፡በስርቆት፡የተሰበሰበ፡ገን
ዘብ፡የጋለሞቶች፡መዝሬኛ፡ይሆናል።—

ገንዘብን፡ለልጅ፡ልጅ፡እንዲተላለፍ፡
ከዋኑ፡ምንጭ፡መቀደት፡ያስፈልጋል።—

፲፪ኛ፡በሰለጠኑት፡አገሮች፡በብልጠ
ት፡የተከማቸ፡ገንዘብ፡በደህና፡ድርጅት፡ስ
ለተከናወነ፡እንደንድ፡ሚኒስቴር፡ቤት፡ወ
ራተኞቹ፡ስለሚያስኪዱት፡ባለቤቱ፡እንደ
ንድ፡አስተዳዳሪ፡ከጥሩ፡ትርፍ፡ሳይ፡ደመ
ወዙን፡ያገኛል፡እንጂ፡ሊሳ፡ትርፍ፡የለውም።

ስለዚህ፡ድርጅቱ፡እንደንድ፡መንግ
ሥት፡ተጠብቆ፡ይኖራል።

ካብታምን፡ በግዕዝ፡ ቋንቋ፡ ባለ፡ጸጋ፡ ይ
ለዋል። ይህ፡ትርጉሙ፡ በእግዚአብሔር፡
ችሮታ፡ ያለ፡ድካም፡ ያገኘ = ማለት፡ነው።

ስለዚህ፡ በጸጋ፡በችርነት፡ ያገኘው
ን፡ እንደዚሁም፡ በቸርነት፡ ለድሆች፡ወ
ንድሞቹ፡ማካፈል፡ይገባዋል፡ይል፡ነበር።

ከዚህም፡ በተቀር፡ አገር፡ካብታም፡
ስትሆን፡ ኅገርም፡ለሕዝብም፡ጠቃሚ፡ይ
ሆናል።

ነገር፡ግን፡ ያንዲንድ፡ ሰው፡የልዩ፡ካ
ብት፡ ለሀገርና፡ለሕዝብ፡ጥፋት፡ነው።

ምክንያቱም፡ ካብታሞች፡ ሲበዙ፡ድ
ሆችም፡ሁለት፡እጥፍ፡ ይበዛሉ።

ካብታሞች፡ካብትን፡ ያገኙት፡በተን
ኰልና፡ በብልጠት፡ ስለሆነ፡ከድሆች፡ያገ
ኙትን፡ገንዘብ፡ ለልጆቻቸው፡ብቻ፡ሲያው
ሉት፡ የድሆች፡ ፈንታ፡ተጠቅሎ፡ ለካብታ





ም፡ ልጆች፡ብቻ፡ ይውላል።

ይልቁንም፡ካብታም፡ገንዘቡን፡ ከ
ራሱ፡ ይበልጥ፡ ስለሚወደው፡ማንንም፡
አያስነካም።

ስለዚህ፡ ያንዳንድ፡ ሰው፡የግል፡ካ
ብት፡ የአገርና፡የሕዝብ፡ መጋደያ፡ክፉ፡
መሣርያ፡ነው፡ ይል፡ነበር።

ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡እንደዚህ፡ይል፡ነ
በር። ባለ፡ጸጋ፡ በዕዉል፡ ያለድካም፡ ያገኘው
ን፡ካብት፡ በከንቱ፡እንደገኘው፡ ለውቹ፡ ለድ
ሆች፡ ወንድሞቹም፡ ማካፈል፡ይገባዋል።

ማለት፡ ካብት፡በድካም፡የሚገኝ፡ቢሆ
ን፡ ከጠዋት፡እስከ፡ማታ፡የደም፡ወዛቸው
ን፡ እያንጠበጠቡ፡ የሚሠሩ፡የቀን፡ሞያተ
ኞች፡ ይከብሩ፡ነበር።

ካብት፡የሚገኘው፡ ባቋራጭ፡ መንገ
ድና፡ በብልጠት፡ ስለሆነ፡ ይህንን፡ በከንቱ፡የ

ቱገኘ፡ገንዘብ፡መድኃኒታችን፡ገንዘባችሁ፡ ባልሆነው፡ገንዘብ፡ወዳጅ፡ግዙበት፡እንደ ሰው፡ሁሉ፡እኛም፡በእግዚአብሔር፡ቸር ነት፡ያገኘነውን፡ብልጽግና፡እንዴንድ፡ሚ ኒስትር፡ቡጅጂ፡ለቤተ፡ሰባችንና፡ለሀገር ድሆች፡ደልድለን፡የቄሣርን፡ለቄሣር፡የ እግዚአብሔርን፡ለእግዚአብሔር፡ማደ ሳደል፡ይገባል፡ይል፡ነበር።

ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡ባለ፡ጸጋነትን፡አ ይነቀፍም።

ነገር፡ግን፡በጣም፡የሚጠላው፡ብል ጽግናውን፡ለራሱ፡ብቻ፡የሚያውልን፡ነው፡

ቅዱስ፡ያዕቆብ፡እናንተ፡ባለ፡ጠጐች፡ አልቅሱ፡ዋይም፡በሉ፡በሚመጣባችሁ፡ መከራ፡ባለጠግነታችሁ፡ጠፍቶዋልና፡ል ብሳችሁንም፡ብል፡በልቶታልና፡ወርቃች ሁም፡ብራችሁም፡ዛገ። ዝገቱም፡ምስክ





ር፡ይሆንባችኋል። ሥጋችሁንም፡ይበላ ዋል፡እንደ፡እሳት፡በሉ፡እንደተናገረው፡የ ቀበርነው፡ገንዘብ፡ፈንድቶ፡እሳት፡ሆኖ፡እ ገርን፡እንዳያጠፋ፡እንድንጠንቀቅበት፡ነ ው።

፲፱ኛ፡ ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡ስለ፡ነፃነ ት፡ነገር፡እንደዚህ፡ይል፡ነበር። ነፃነት፡ማ ለት፡በሀገሩ፡ሳይ፡በሕግ፡የተሰጠውን፡መ ብቱን፡ለመሥራት፡መቻል፡ነው።

ነፃነት፡በሁለት፡አኳኋን፡ይገለጻል። አንደኛው፡በራሱ፡ንጉሥ፡ነገሥትና፡በመን ግሥቱ፡ሕግ፡በታች፡ሆኖ፡መብቱን፡መፈጸ ም፡ነው።

ሁለተኛው፡ነፃነት፡ሕግ፡በሚፈቅደ ው፡መጠን፡የሰው፡ልጅ፡ሙሉ፡ነፃነትን፡እ ንዲያገኝ፡ነው። ይህ፡ሲሆን፡ቮልቴር፡የሚ ባል፡የፈረንሳዊ፡ጸሐፊ፡ሰው፡ሁሉ፡ነፃነት

ን፡ማግኘት፡ይገባዋል። ነገር፡ግን፡የጐረቤቱን፡ነፃነት፡ሳይደፈርና፡ወንጀሉን፡ሳያስቀይም፡መሆን፡ይገባዋል፡ይላል።

ስለዚህ፡ለሰው፡ልጆች፡የሀገርና፡የመንፈስ፡ነፃነት፡ማግኘት፡ይገባቸዋል፡እንራ፡ነፃ፡የሆነ፡ሕዝብ፡የሚገባውን፡ነፃነት፡ካላገኘ፡ነፍስ፡የሌለው፡ሥጋ፡ማለት፡ነው።

ለሀገር፡ነፃነት፡ጠቃሚ፡የሚሆኑ፡ገንዘብና፡ኃይል፡ሲሆኑ፡እንዲሁም፡ለመንፈስ፡ነፃነት፡ትምህርትና፡እውቀቶች፡ናቸው፡ይላል፡ነበር።

ይልቁንም፡ነፃነት፡ለሰው፡ልጅ፡መሉ፡መሣሪያ፡ስለሆነ፡የሰው፡ልጅ፡ጥቂት፡በጥቂት፡የከበረ፡ፍጥረት፡መሆኑን፡በትምሕርት፡ስለሚያውቅና፡በመንፈሱ፡ባሪያ፡አለመሆኑን፡ስለሚረዳ፡እውነትን፡ይዞ፡መፍረድና፡የሰውን፡ፊት፡አለማየት፡እውነ





ትን፡ያስተምረዋል።

የሰው፡ልጆች፡በሀገር፡ነፃነት፡ምክንያት፡የመንፈስንም፡ነፃነት፡ያገኛሉ።

ስለዚህ፡ሰው፡ትልቅ፡መሆኑን፡ሳያውቅ፡ልብ፡የሌላቸውን፡እንስሶች፡መስሎ፡ያለውን፡የትዬስ፡ዴዊትን፡ሬሳዞሬ፡በመልከት፡ሰው፡ትልቅ፡ፍጥረት፡መሆኑን፡ለማሳወቅ፡መድኃኒቱ፡ትምህርት፡ብቻ፡ነው፡በተቀረ፡ዕንቍህን፡በሬያ፡ሬት፡አትጣል፡እንደተባለው፡ባልተማረ፡ሕዝብ፡በኩል፡የነፃነት፡ዋጋ፡እንደማትታወቅ፡አይጠረጠርም፡ይል፡ነበር።

፲ኛ፡ልጅ፡ደስታ፡ተሰማ፡ስለ፡ሞትነገር፡በጣም፡ይገረም፡ነበር።

ምክንያቱም፡ሞት፡በመካከላችን፡ሲኖር፡ከኛ፡እንደ፡በተነጠቀ፡ጊዜ፡ብቻ፡ነው፡የምናውቀው። ፀሐይንና፡ሞትን፡ትኩር፡ብ

ለን፡ አይተነው፡ እንደማናውቅ፡ እንደዚሁ ዓም፡ ሞት፡ በመካከላችን፡ ተለምዶ፡ ይኖራል፡

የሰው፡ ሕይወት፡ እንደ፡ አረሩ፡ እንደ፡ አበባ፡ እንደ፡ ጥላ፡ መሆኑን፡ አያውቅን፡ እንኖ ራለን፡ በማለት፡ መጋረጃ፡ ስለተሸፈነ፡ የሰው፡ ልጅ፡ በሩቅ፡ አሳቤ፡ በትርጉ፡ ቅሬ፡ ሆኖ፡ ሳይ ሰማው፡ ይኖራል።

ባንድ፡ ገዳም፡ እንድ፡ በቅድስና፡ የሚኖ ሩ፡ መነኩሴ፡ ሌሊቱን፡ ሁሉ፡ በመጨነቅና፡ በ ኃዘን፡ ያሳልፉት፡ ነበር።

እንዲት፡ ሌት፡ ምን፡ ጣም፡ ያለው፡ እንት ልፍ፡ አግኝተው፡ አያውቁም።

ስለዚህ፡ እንድ፡ የሳቸው፡ ደቀ፡ መዝሙ ር፡ የሆነ፡ መነኩሴ፡ አባቴ፡ ምነው፡ እንቅልፍ ን፡ ያህል፡ የሰው፡ ልጅ፡ ዕረፍት፡ ትተው፡ ሌሊ ቱን ——— ሁሉ፡ ሲያዝኑ፡ ያድራሉ፡ ብሎ፡ ቢጠይቃቸው፡ መነኩሴው፡ ልጄ፡ ሆይ፡ ሞ





ትን፡ ያህል፡ እሹህ፡ በመኝታዬ፡ ሳይ፡ ተከስ ክሶ፡ እንደምን፡ ልተኛ፡ ብለው፡ መለሱላ ቸው፡ ይባላል።

ይህ፡ እውነት፡ ነው፡ በሞት፡ ሁሉን፡ እን ተዋለን።

በሞት፡ ወዳጅን፡ ካብትን፡ ደስታን፡ ቤ ት፡ መንግሥትን፡ መንደሮችን፡ ጉጆችን፡ ከ ሰው፡ አርትን፡ የምንኖርበትን፡ የጸጥታ፡ ር ስታችንን፡ ቤት፡ ዘመዶቻችንን፡ ፍቅርን።

በዚህ፡ በሚያሳዝን፡ በወኅኝ፡ ድንገት ኛ፡ ጥሪ፡ የፍጻ፡ ጊዛችንን፡ አየጉተትን፡ እን ጊዛለን።

ሰው፡ ከፉም፡ ቢሆን፡ ደግ፡ የድካሙ ፍሬ፡ ተድሞ፡ ይቆየዋል።

በዚህ፡ በጥቂት፡ ዘመን፡ ከዓለም፡ ጋር፡ ተሳስሮ፡ የነበረ፡ ሰው፡ ጊዜውን፡ አየጉተተ፡ በ ብዙ፡ ድካም፡ ወደማትቀር፡ ፈጣን፡ በሆነች፡

የፍቅር፡መሪ።

በዲቲቻ፡ጥሪ፡ውለጥ፡ከሚያውቀው፡ና
ለም፡ይለያል።

ሰው፡ሆዱ፡በዚያን፡ጊዜ፡የሚወድ
ሀ፡የለም። ስምህም፡እንዲሞት፡ሰው፡
ክልብ፡ይረሳል።

ነገር፡ግን፡የማትረሳው፡በዚህ፡ዓለ
ም፡ሳለህ፡ጊዜህን፡ሳታባክን፡ለችግረኞች፡
ወንድሞችህና፡ለሀገርህ፡ለንጉሠ፡ነገሥ
ት፡መንግሥትህ፡የዲከምከው፡ብቻ፡ነው።

እካልህ፡በስብሶ፡ወዲ፡መሬትነቱ፡ሲ
መለስ፡የሠራኸችው፡በጐ፡ሥራዎች፡ለ
ምልመው፡አብበው፡ፍሬ፡አፍርተው፡ሰ
ለሚታዩ፡ከመቃብር፡በሳይ፡ለሚቀሩ፡
ሥራዎች፡ብቻ፡ድክም፡እያለ፡ያዝን፡ነበር

እንባቢ፡ሆይ።

የልጅ፡ዲስታን፡ሬሎዞሬ፡ለመጻፍ፡ብ
ዙ፡ጊዜ፡ሰለሚፈጅ፡በዚሁ፡እንቁም።